ስም፡ ኃይሌ ፊዳ ኩማ /መላኩ/

ሥራ ሕዝብ ድርጅት ጽ/ቤት

እድሜ፡ 38 ዓመት

አድራሻ፡ አዲስ አበባ ከተማ

ሥምና አድራሻዬ ከዚህ በላይ የተመዘገበው ዛሬ ጳጉሜን 2 ቀን 1969 ዓ.ም ከቀኑ 7 ሰዓት ተኩል ሲሆን ታላቁ ቤተ መንግሥት ደርግ ምርመራ ክፍል ቀርቤ ከዚህ የሚከተለውን የተከሣሽነት ቃሌን እሰጣለሁ ::=

በ1932 ዓ.ም ከአባቴ ከአቶ ፊዳ ኩማና ከእናቴ ከወ/ሮ ጉዲኔ ደጋ ተወልጄ እድሜዬ ለትምህርት ሲደርስ ከ1ኛ ክፍል እስከ 5ኛ ክፍል ድረስ በወለጋ ክፍለ ሐገር አርጆ አውራጃ ቢትወደድ መኩንን ት/ቤት ተምሬ ከዚያ ወለጋ ክፍለ ሐገር ለቀምት ከተማ ቀ.ኃ.ሥ ት/ቤት ገብቼ እንደገና 5ኛ ክፍል በመግባት ከ5ኛ እስከ 7ኛ ክፍል ድረስ ተምሬ እዚያው ወለጋ 7ኛ ክፍል እያለሁ የ8ኛን ክፍል የሚኒስትሪ ፈተና ተፈትኜ በማለፌ አዲስ አበባ በ1946 ዓ.ም ጄኔራል ውንጌት ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ገብቼ ለ5 ዓመት ያህል ከተማርኩኝ በኋላ በመምህርነት ከት/ቤት እንደወጣሁ በሐረርጌ ክፍለ ሐገር ደደር ከተባለው ከተማ አንድ ዓመት አስተምሬ በ1953 ዓ.ም አዲስ አበባ ከተማ በሚገኘው ቀ.ኃ.ሥ ዩኒቨርስቲ ገብቼ 4 ዓመት ከተማርኩ በኋላ በዚሁ ዩኒቨርስቲ ውስጥ የኬሚስትሪና የፊዚክስ መምህር በመ ሆን

../...

ለአንድ ዓመት አስተምሬ ስኮላር ሺፕ በማግኘቴ ለትምህርት ወደ ፈረንሣይ አገር ለ3 ዓመት ሄድኩ፤ እዛም ሄጄ አሣተፍ፡ የነበረው ትምህርት ሁ... ዲፕሎ ፊዚክስ ፤ ሌ ለሁለት ዓመት ደግሞ ሦሥለኛ ተምሬ ዱግሪውን እንደተቀበልኩ የኢትዮጵያ መንግሥት ፓስፖርቴን ሠረዘው፤ ስኮላር ሺፑም ተቋረጠ ፓስፖርቱ ሲሠረዝና ስኮላር ሺፑም ሲቋረጥ የበቃው በአውሮፓ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማኅበር ውስጥ አባል ከመሆኔም በላይ፡ የማኅበሩ መሪ ስለነበርኩ የንጉሠ ነገሥቱንም አመራር ስለምቃወም በዚህ ምክንያት ተሰረዘ ::

እኔም በፈረንሣይ ውስጥ አሉስ ናሽናል ደሳንዚ ስር የንታል

/

/ ትምህርት ቤት በወር $400 ብር እየተከፈለኝ ለሁለት ዓመት ያህል አስተምሬ ጀርመን አገር ያለው ተራማጅ የኢትዮጵያ ኤምባሲ ፀሐፊ የነበረው አቶ ዓለማየሁ አበበ የተባለው በደብዳቤ በላከልኝ ፓስፖርት አማካይነት ከፓሪስ ወደ ምዕራብ ጀርመን እንደ ኢት. አቆጣጠር በ1970 ዓ.ም መጨረሻ ላይ ሄጄ የሐምቡርግ ዩኒቨርስቲ ኃላፊ የሆነውን ዶ/ ሐመሽ ሚት የተባለውን ጀርመናዊ አግኝቼ በዚሁ ዩኒቨርስቲ ውስጥ ለ2 ዓመት ያህል በወር $2000 ብር እየተከፈለኝ ሣስተምር ቆይቼ በጥር ወር 1967 ዓ.ም ወደ ኢትዮጵያ ተመ ለስኩኝ ::

በለውጡ ምክንያት በመንግሥት ውሣኔ አብዮታዊ እርምጃ የተወሰደበት ወይም በእስር ላይ ያለ ዘመዱ የለኝም ፤ በለውጡ ምክንያት በመንግሥት ውሣኔ የከተማ ቤትና በታ ፤ የገጠር መሬት ለሰፊው ሕዝብ ሲሆን ከእኔም ሆነ ከቤተሰቦቼ የተወሰደ ምንም ነገር የለም ::

ዘመቻ ስለማይመለከተኝ አልዘመትኩኝም እናትና አባቴ በሕይወት አሉ ያሉትም በወለጋ ክፍለ ሃገር አርጆ ከተባለው አውራጃ ውስጥ ሲሆን፡ የሚተዳደሩት አባቴ አናጢ ስለሆኑ ወንበርና ጠረጴዛ ሠርተው በመሸጥ በሚያገኙት ገንዘብ ነው ::

አባቴ ወንበርና ጠረጴዛ ሠርተው በሚያገኙት ገንዘብ 5፣ ቤተ ሰብ ያስተዳድራሉ ፤ ወንድሞቼ 3 ሲኖሩኝ አንዱ ታደሰ ፊዳ የተባለው መምህር ነው፤ እህቶቼም 3 ሲኖሩኝ ሁለቱ ባል ያገቡ ሲሆን አንዷ የ1ኛ ክፍል

ተማሪ ናት ፡ የቀሩት ሁለቱ ወንዶቼና አንዷ እህቴ ሥራ የላቸውም ፣ አቤም ሆኑ ሥራ የሌላቸው ወንዶቼ የሚተዳደሩት እኔ በምረዳቸው $100 ብርና ወንዶቹ በሚያደርጉላቸው በዘቀን የማለውቀው የገንዘብ እርዳታ ነው ።

ለእኔ መንግሥት በወር $980 ብር የሚከፍለኝ ሲሆን ለትምህርት ታክስ ፣ ለጡረታ ፣ ለእናት አገር ጥሪ ለዘመቻት ተቀንሶ በእጄ $721 ብር ይደርሰኛል ። ከዚህም ውስጥ ለአባቴ እና ለእናቴ $100 ብር ልኩ $621 ብር ይቀረኛል በዚህ በማገኘው ገንዘብ ማንንም አላስተዳድርም እራሴን ብቻ ነው ።

በኢትዮጵያ ውስጥ ሚስት አላገባሁም ግን ፈረንሣይ አገር በነበርኩበት ወቅት ማሰነ የተባለች ባለቤት ነበረችኝ ፣ ከእሷም 1ኛ ሣራ ኃይሉ ፣ 2ኛ/ ዮዲት ኃይሉ የተባሉትን ሁለት ልጆች አስወልጄ እነሱም በፈረንሣይ አገር ይገኛሉ ። ለእነዚህ ልጆች በወር ከማገኘው ደመወዝ ምንም የምልክላቸው ገንዘብ የለም ግን አንዳንድ ጊዜ የሚሄዱ ሰው ሣገኝ የሐገር ልብስ እየገዛሁ እልክላቸዋለሁ ።

ወደ ኢትዮጵያ በምመጣበት ወቅት ባለቤቴንና ልጆቼን ይዤ አለመጣሁም ምክንያቱም እኔ እስከደላደልና ለባለቤቴም በኢትዮጵያ ውስጥ ተመጣጣኝ ሥራ እስካገኝሁ ጊዜ ድረስ ነበር ፣ ለባለቤቴ ሥራ ለማግኘት ሞክሬ ነበር ግን ለማግኘት አልቻልኩም ፣ የጠየቁሁትም ሲሴ ት/ቤት ውስጥ ነበር ።

እ.ሄ የመ.ኢ.ሶ.ን መሥራች አባል ስሆን ይህንንም ድርጅት የመሰረትኩት አንድ ኤውሮፓ አቆጣጠር በ1968 ዓ.ም ምዕራብ ጀርመን ውስጥ ሆኜ ነው ።

የመሠረትነው አባሎች ፡=

| | |
|---|---|
| 1ኛ/ ጠጉስ ገብረ የሱ | 6ኛ/ ወርቁ ፈረደ |
| 2ኛ/ ዳንኤል አደራ | 7ኛ/ ቢሣይ ታከለ |
| 3ኛ/ ነገደ ጉበዜ | 8ኛ/ ተፈራ ወንደ |
| 4ኛ/ እንዳርጋቸው አሰግድ | 9ኛ/ ምትኩ በላቸው |
| 5ኛ/ ፍቀሬ መርደ | 10ኛ/ ኃይሉ ፊጫ |

11ኛ/ ያዩ ይራዱ ቀጣው
12ኛ/ አሰፋ ገብረ ሥላሴ
13ኛ/ ግርማ በሻህ
14ኛ/ መለስ አያሌው
15ኛ/ ደሣለኝ ራህመቶ
16ኛ/ አለሙ ፈለቀ
17ኛ/ ከበደ መንገሻ
18ኛ/ አብዱላሂ ዩሱፍ
19ኛ/ ከድር መሐመድ ነበርን፡=

ከእነዚህም አባሎች መሐል ድርጅቱ ያስወጣቸው አባሎች 1ኛ/ ጡጌስ ገብረ የሱስ ፣ 2ኛ/ ዳንኤል አደራ ፣ 3ኛ ተፈራ ወንዴ፣ 4ኛ/ ያዩ ይራደ ቀጣው ፣ 5ኛ/ ግርማ በሻህ ፣ 6ኛ/ መለስ አያሌው ፣ 7ኛ/ ደሣለኝ ራህመቶ ሲሆኑ ፣ አለሙ ፈለቀ የተባለው ከድርጅቱ መውጣት ያለመውጣቱን አላውቅም፣ ከዚህ በላይ የጠቀስኳቸውና ከድርጅቱ የተወገዱት አባሎች በድርጅቱ ውስጥ ዲሲፕሊን ባለማክበራቸውና በድርጅቱ የፖለቲካ መስመር ባለመስማማታቸው የተወገዱ ናቸው ::

በድርጅቱ ማለት በመ.ኢ.ሶ.ን ውስጥ ከመመስረቱ ጀምሮ እስካሁን ድረስ በመስራት ላይ ያሉ አባሎች :=

1ኛ/ ዶ. ነገደ ጎበዜ /ነጋሽ/
2ኛ/ አቶ አንዳርጋቸው አሰግድ /ወለዬ/
3ኛ/ አቶ ሲሣይ ታከለ /አሸናፊ/
4ኛ/ አቶ ኃይሌ ፊዳ /መላኩ/
5ኛ/ ዶ. ከበደ መንገሻ / ነጋ/ ሲሆኑ እነሱም በጠገር ውስጥ በመሥራት ላይ ያሉ የድርጅቱ አባሎች ናቸው ::

በድርጅቱ ሥራ ላይ እያሉ በሞት የተለዩ አባሎች ያሉ ሲሆን እነሱም := 1ኛ/ አቶ ፍቅሬ መርዕድ / ሣሙኤል/ ፣ 2ኛ/ አቡዱላሂ ዩሱፍ / አደም/ ናቸው ::

በአውሮፓ ውስጥ እንዳለን ከላይ ከጠቀስኳቸው 18 ሰዎች ጋር ሆነን መ.ኢ.ሶ.ንን ለመመስረት ተስማምተን ፕሮግራምና ደንብ አዘጋጅተን

../:.

ያንዳንዱ አባላት የጥናት ክበብ ከፍቶ ካስጠና በኋላ አባላትን መመልመል ይጀምራል ፤ በዚህ ዓይነት ሁላችንም የጥናት ክበብ ከፍተን በማስጠናት መመልመል ጀምረን ሥራውን ማካሄዱ እንደጀመርን በ1966 ዓ.ም የኢትዮጵያ አብዮት ፈነዳ ፤ እኔም ከጓደኞቼ ጋር ቀደም ሲል ወደ ኢትዮጵያ ለመምጣት ዕቅድ ስለነበረኝ የአብዮቱ መፈንዳት አጋጣሚ ስለሆነ ፤ 1ኛ/ አቶ አንዳርጋቸው አሰገደ ፤ 2ኛ/ እኔ አቶ ኃይሉ ፊዳ ፤ 3ኛ/ ዶ. ነገደ ጎበዜ ሆነን በቀደም ተከተል ወደ ኢትዮጵያ ተመለስን ከመጣን በኋላ መ.ኢ.ሶ.ንን በኢትዮጵያ ውስጥ ማደራጀት ጀመርን ፤ እኔም እንደመጣሁ የመ.ኢ.ሶ.ን አባላት በሙሉ ተሰብስበን ገንዘብ በማዋጣት 4 ኪሎ ያለውን ተራማጅ መጽሐፍት ቤት በመክፈት እዛው እየሰራሁ በወቅቱ ጉልቶ የሚታየው ኢ.ፒ.አር.ፒ ስለነበር እሱን ለመቋቋም የማርክስስንና የሌኒንን መጽሐፍቶች በገጠር ላለው ዘማችና ለማናቸውም እንዲደርስ ማድረግና በተለይም የሰፊው ሕዝብ ድምጽ የሚለውንም ጋዜጣችን በዚሁ ዓይነት ማሰራጨት ጀመርን ። ከዚህ በኋላ ቀስ በቀስ መ.ኢ.ሶ.ን. መታወቅን አፈራ ፤ እኛም ለየአንዳንዳችን ቀድሞ የነበረንን የሥራ ክፍፍል ይዘን መምራት ጀመርን ።

የሥራ ድርሻችን 1ኛ የእኔ የኃይሉ ፊዳ ፤ 2ኛ/ የአንዳርጋቸው አሰገዱ ፤ 3ኛ/ የዶ. ነገደ ጎበዜ ፕሮፓጋንዳና ቅስቀሳ ።

1ኛ/ ዶ. ከበደ መንገሻ ።

2ኛ/ አቶ ሲሣይ ታከለ

3ኛ/ ዶ/ ወርቁ ፈለቀ ሆነው የድርጅቱን ሥራ እያከናወኑ ካሉት አባላት ላይ የሚሰበሰበውን ወራዊ መዋጮ ተረክበው ለድርጅቱ ማስረከብ ነበር ፤ መ.ኢ.ሶ.ን በዛን ወቅት በመንግሥት ደረጃ አይታወቅም ነበር ፤ የምናካሂደው እኛ በስውር ነበር ፤ በኋላ መንግሥት ውጭ አገር ስነበርንበት ወቅት በተማሪዎች ማኅበር ታዋቂነት ስለነበረንና ወደ ሀገራችንም መግባታችን ስለሚያውቅ ። 1ኛ/ ለእኔ ለአቶ ኃይሉ ፊዳ ፤ 2ኛ/ አቶ አንዳርጋቸው አሰገዱ

3ኛ/ አቶ ባሮ ቱምሳን በጥር ወር 1967 ዓ.ም ደርግ ጽ/ቤት ተጠርተን ሻ/አለቃ ዓለማየሁ ፣ ሻምበል ፍቅረሥላሴ ወግደረስ ፣ ሻለቃ ደምሴ ደሬሳ ሆነው መንግሥት አንድ ፓርቲ ለማቋቋም አስቧልና እናንተ የምታውቋቸውን ተራማጅ ሰዎች በሙሉ ሰብስባችሁ የፓርቲውን አስኳል እንድትፈጥሩ ነው የጠራናችሁ በማለት አነጋገሩን. እኛም መልስ ስንሰጥ በአሁኑ በኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ አንድ ፓርቲ ማቋቋም ትክክል ስላልመሰለን መጀመሪያ የዲሞክራሲ መብቶች ተፈቅደው ተራማጆች ሁሉ እንደደራጁ ማገዝ ይሻላል የሚል ሃሣብ ታቀረብን ፣ ከዚህም ሌላ መንግሥት ተራማጅ የሆኑትን ቡድኖች በአንድነት እንዲሰበሰቡ አድርጎ አንድ ፓርቲ ሊፈጥር ይችላል ስንላቸው አሸ፡ ልናሰብበት እንችላለን፡ ብለው ቀጠሮ ሰጥተውን ሄዱን ። ከዚያም በየካቲት ወር 67 ዓ.ም መጥተን ከላይ ከጠቀስኳቸው መኰንኖች ጋር ተገናኝተን ባደረግ ነው ውይይት ከሻምበል ዓለማየሁ ኃይሌ የቀረበው ሃሣብ ተራማጆች ተሰብስበው ፖሊት ቢሮ ይቋቋም የሚል ነበር ።

በእኛ በኩል ደግሞ የቀረበው ሃሣብ የሚቋቋመው ተቋም ፓሊት ቢሮ ከሚሆን ፡-

ሀ/ የኅብረተ ሰብአዊነትን የሚያስፋፋ ፣

ለ/ የሰፊውን ሕዝብ መደራጀት የሚያግዝ ጽ/ቤት ቢቋቋም ይሻላል፡ የሚል ሃሣብ አቅርበን ይህም ተቀባይነት አግኝቶ የሕዝብ ድርጅት ጽ/ቤት ታህሣሥ 18 ቀን 1968 ዓ.ም ተቋቋመ ፣ እኛም ከመንግሥት ደመወዝ እየተከፈለን የሕዝብ ድርጅት ጽ/ቤት አባሎች ሆነን ፣ በዚህ የተነሣ መ.ኢ.ሶ.ን ከጊዜአዊ ወታደራዊ መንግሥት ጋር ተዋወቀ ።

የሕዝብ ድርጅት ጉዳይ ጊዜአዊ ጽ/ቤት ከተቋቋመ ወዲህ በድርጅቱ አማካይነት ወዟደሩና አርሶ አደሩ በ1968 ዓ.ም መጀመሪያ ላይ በወጡት አዋጆች አማካኝነት እንዲደራጁ ቅስቀሣ አካሂደናል ። እንዲሁም ወጣቶችና ሴቶች በየበኩላቸው እንዲደራጁ ለማድረግ ጥረት ተደርጓል ። ይህንን ቅስቀሣ በምናደርግበት ጊዜ ዋናው ሥራችን ኢ.ሕ.አ.ፓ ቀድሞ ከገባባቸው ሕዝባዊ ድርጅቶች ውስጥ ተጋለጡ እንዲወጡ ማድረግ ነበር ። በሌላ በኩልም የቦሻሌ

ባሥን ቅልበፋና ለማስፋፋት በሕዝብ ድርጅት ጉዳይ ጊዜአዊ ጽ/ቤት የፍልስፍናና የማስታወቂያ ኮሚቴ አማካኝነት ::

1ኛ/ በየሁለት ሣምንት የሚታተም መጽሔት "አብዮታዊት ኢትዮጵያ"

2ኛ/ በልዩ ልዩ አርዕስቶች ላይ ትንንሽ መጽሐፎች በማዘጋጀትና በሰፊው በማሰራጨት የሰፊው ሕዝብ ንቃተ ሕሊና ከፍ እንዲል ለማድረግ ጥረት ተደርጓል ::

በሦስተኛ ደረጃ ለጊዜአዊ ወታደራዊ መንግሥት በልዩ ልዩ የአገሪቱና የአብዮት ጥያቄዎች ላይ ጥናቶችንና ሃሳቦችን አቀርበናል ::

በሰኔ 1968 ዓ.ም በሕዝብ ድርጅት ጉዳይ ጊዜአዊ ጽ/ቤትና በተለይም ጽ/ቤቱን ስሞኖጋል ይዘታል ተብሎ በተገመተው መ.ኢ.ሶ.ን ላይ ቀጥታ የሆነ ተቃውሞ በወታደራዊ ካድሬዎች አቋም ተወሰደ :: ይህንን ተቃውሞ የጊዜአዊ ወታደራዊ መንግሥት ሊቀ መንበር ሌ/ኰሎኔል መንግሥቱ ኃይለማርያምና ሻምበል ዓለማየሁ ኃይሌ ለወታደራዊ ካድሬዎቹ ተገቢ ያልሆነ አቋም ነው ብለው ገልጸውላቸው ነገሩ በዚህ ተዘጋ :: ይሁንና በሌሎች የሕብረት አባላት በተለይም በወዝ አደር ሊግ በኩል በወታደራዊ ካድሬዎች የተሰነዘረው ተቃውሞ እንደቀጠለ ነበር :: በመስከረም 1969 ዓ.ም ኢ.ሕ.አ.ፓ በቀጥታ ወደ ነፍስ ግድያ ተዛወረ፤ የሕዝብ ድርጅት ጉዳይ ጊዜአዊ ጽ/ቤት አባሎችን መግደል ጀመረ ፣ ይኸው ሁኔታ ተፋፍሞ እንዳለ በጥቅምት ወር የደርግ የአቋም ለውጥ ጥናት ተጀመረ ፣ እንደሚታወቀው በዚህ የአቋም ለውጥ ውስጥ አነ ዓለማየሁ ኃይሌ ቁልፍ የሥልጣን በታዎችን ያዙ :: ወዲያውኑ በመ.ኢ.ሶ.ን ላይ ቀጥታ ዘመቻ ጀመሩ :: ከዚህ በፊት ግን በመስከረም ወር 1969 ዓ.ም ከአነ ዓለማየሁ ኃይሌ ጋር በጽሁፍ ከፍተኛ ክርክር አደረገን ፣ በኋላም አነ ዓለማየሁ ኃይሌ ሥልጣን ካገኙ በኋላ በይበልጥ በመ.ኢ.ሶ.ን ላይ ተቃውሟቸውን አባባሱት ፣ ነገር ግን ይህ ተቃውሞ መ.ኢ.ሶ.ን ብቻ የሚመለከት ሳይሆን ፣ ሰደድ፣ ሊግ ፣ ኢጭአትና ማሌሪድ ተግባራዊ ግንባር ተፈጠረ :: ይህም አማካኝነት በሰፊው ሕዝብ ውስጥ በደርግ ውስጥ ስለተፈጠረው አዲስ ሁኔታ ቀስቀሣ ለማድረግ ተቻለ :: በጥር 21 ቀን 1969 ዓ.ም ቋና

ሊቀ መንበር የነበሩት ብ/ጄኔራል ተፈሪ ባንቲ ባደረጉት ጥሪ ውስጥ ኢ.ሕ.አ.ፓ በፍጹም በፀረ አብዮተኛነት እንዲጠራ ተደረገ። ጥር 22 ቀን 1969 ዓ.ም በተደረገው ሠላማዊ ሰልፍ ላይ ሰፊው ሕዝብ የጠቆና ተራማጅ ችን መፈክሮች በመቀበል ኢ.ሕ.አ.ፓን ከማውገዙም በላይ የጄኔራል ተፈሪን ንግግር ተቃወመው ። ጥር 24 ቀን 1969 ዓ.ም በዩኒቨርስቲ ተማሪዎች ስብሰባ ላይ ጠቆና ተራማጆች ተዘጋጅተው በመጡ የኢ.ሕ.አ.ፓ ወገኖች ላይ የጥቃት እርምጃ ወሰዱ ። ይህ እርምጃ በእነ ሻምበል ዓለማየሁ በኩል የነበረውን ተቃውሞ አፋጥኖት የዚያኑ እለት የሕዝብ ድርጅት በተለይም የመ.ኢ.ሰ.ን አባሎች ወንጀሎች የሚመረምር ኮሚቴ አቋቋሙ ተባሉ ። ጥር 26 ቀን 1969 ዓ.ም በእነ ዓለማየሁ ላይ እርምጃ ተወሰደ ።

ከዚህ በኋላ አንዳንድ የአዲስ አበባ ቀበሌዎችና ወዝ አደሮች እንደታጠቁ ተደርጉ በየቦታውና በየድርጅቱ ያሉ የኢ.ሕ.አ.ፓ አባሎች እንዲጋለጡና እንዲያዙ በመደረጉ አብዮቱ በተከላካይነት ወደ አጥቂነት ተሸጋገረ ። ከዚሁ ጋር በማከታተል በአዲስ አበባ ከተማ አሰሳ ተካሄደ የፀረ አብዮተኞች መሣሪያዎች ሲያዙ እንዲሁም የታወቁ አናርኪስቶች በብዛት ታሰሩ ። ከዚህ አሰሳ በኋላ በመ.ኢ.ሰ.ን ላይ ከሌሎች የሕብረት ድርጅቶች አንዳንዱ ተቃውሞዎች መሰማት ጀመሩ ። ከነዚህም ውስጥ በአሰሳው የተገኙትን መሣሪያዎች መ.ኢ.ሰ.ን ወሰዷቸዋል የሚል ነበር ። በአጠቃላይም በሕብረቱ አባሎች መጠሉም አለመግባባትን ስለተፈጠረ ከመጋቢት ወር መጨረሻ ጀምሮ አብዮቱ እንደገና ወደ ተከላካይነት እንዲመለስ ተደረገ ። ይህም የሆነው ሰፊውን ሕዝብ የሚያስታጠቅ ነገር ስለቆመና በሌላው በኩል ደግሞ ሰፊው ሕዝብ የወሰዳቸውን ነፃ እርምጃዎች በመንግሥት በኩል ተቀባይነትን ስላላገኙ ነበር ።

በሚያዝያ 23 ቀን 1969 ዓ.ም የወዝ አደር ቀን ሲከበር ዝግጅት ሲደረግ ዝግጅቱን የሚያቀነባብር አንድ የሕብረት ኮሚቴ ተቋቋመ ። ይህ ኮሚቴ የተቋቋመው ከኢ.ጭ.አ.ት በቀር የአራቱ ድርጅቶች አባላት የተገኙበት ሆኖ ነበር ። በዚህ ኮሚቴ ውስጥ ለዝግጅቱ የሚሆን ልዩ ልዩ ፖስተሮችን እርማዎችን ለማዘጋጀት ከየድርጅቶቹ ገንዘብ ተዋጥቶ ነበር ። በኮሚቴው

ውስጥ የነበረው ስምምነት የሕብረት አርማዎችን አስቀድሞ ከእነሱ በስተጀርባ ግን አያንዳንዱ ድርጅት የየራሱን አርማዎችና መፈክሮች ለመያዝ እንደሚችል ነበር ። በዚህ መሠል ሚያዝያ 22 ቀን 1969 ዓ.ም በድሬዳዋ ከተማ በመ.ኢ.ሶ.ን ድርጅት ጓዶች በኩል የተደረገው ዝግጅት የመ.ኢ.ሶ.ን አርማ በብዛት የያዘ ስለነበረ እንዲሁም የመ.ኢ.ሶ.ን አርማዎች ያሉባቸውን ሸራዎች አንዳንዶቹ ተሰላፊዎች እንዲለብሱ ዝግጅቱ ተደርጎ ስለነበር ይኸው ጉዳይ እዚያ ካሉት የደርግ አባሎች/ሊቀመንበሩ ተነገሮ ይህ ዝግጅት እንዲታረምና የሕብረቱ አርማዎች እንዲያዙና ድርጅቶችም የየራሳቸውን ይዘው እንዲወጡ ሸራው ግን እንዲቀር ለድሬዳዋ መመሪያ ተሰጠ ። በዚህ መሠረት እዚያ ያለው የደርግ አባልና እዚያ የነበረው ጓድ አብዮታዊ ዩሱፍ በተቀበሉ ውና ድርጅቶች እየዘሩ የሚወጡትንና የሚቀሩትን አርማዎችና መፈክሮች ለይተው በዓሉ በዚህ መንገድ ተባበረ ።

አዲስ አበባን በሚመለከተው በኩል በተለይም ሊቀመንበሩ ለእኔ ከደወሉልኝ በኋላ በበኩሌ የአርማዎቹ መውጣት እንዲቀር ሃሳብ አቀርቤ፤ በዝግጅት ኮሚቴ ውስጥ የነበሩት ጓድ ነገደ ጎበዜና ጓድ ተስፋዬ መኩንን ሣማክራቸው ዓርማዎቹ ከተሰራው በኋላ በማግስቱ ለሚደረገው ሠልፍ እንዳይወጡ ለማድረግ አስቸጋሪ ነው ተባለ ። ይኸው ጉዳይ ለጄ አለቃ ለገሠ ተገልጦለት፣ ቀዳሜ ዕለት ወደ ሰባት ሰዓት ላይ እንደገና የሕብረቱ ዓርማዎች ቀድመው ከነሱ በስተጀርባ ሌሎች አርማዎች ማለት የድርጅቶቹ መውጣት ይችላሉ ከሚል ስምምነት ላይ ተደረሰ ። በዚሁ መሠረት በዓሉ አዲስ አበባ ላይ ተከናወነ ፡ ይሁንና በበዓሉ ላይ የመ.ኢ.ሶ.ንና የማሌሪድ በብዛት ስለነበሩ በተጨማሪም አንዳንድ ቡድኖችና ግለሰቦች መ.ኢ.ሶን ፓርቲያችን ነው ፣ መኢሶን አስታጥቅናል የሚሉ መፈክሮችን አሰምተው ስለነበረ ይኸው በሕብረት ጓዶቻችን በኩል ትልቅ ቅሬታዎችን ፈጠረ ። በተለይም አንዳንድ የሰደዱ ጓዶች በኃይለኛ ንዴት መኢሶን ራሱን አጋለጠ ፣ ሌላው ኢ.ሕ.አ.ፓ ነው ፣ እኛ ወታደሮች ነን ደማችን ይፈሰስ እንመታቸዋለን እስከማለት ደረሱ ። መኢሶን ግን በበኩሉ በበዓሉ ከንውን ላይ ስለተደረጉት ስህተቶች ግለሂስ አድርጎ እንዱ የ

../...

ሠራዊት ሕዝብ ድምጽ ቁጥር 54 ይመስለኛል አወጣ ። ይሁን እንጂ በመ.ኢ.ሶ.ንና በሌሎቹ ድርጅቶች መሐል የነበረው መቃቃር /አለመግባባት/ ሊሻሻል አልቻለም ። እንዲያውም በአንዳንድ መ/ቤቶችና የመንግሥት ድርጅቶች ውስጥ በሚደረገው ግለጻ ላይ መኢሶን ሌሰው ኢ.ሕ.አ.ፓ ነው ፤ በቀርቡ ይመታል በማለት የሰደድ ጓዶች በግልጽ ይናገሩ ጀመር ። በተጨማሪም የአዲስ አበባ የሕዝብ ድርጅት አባሎች በተለመደው መሠረት ግለጻዎችን ከማድረግ ታገዱ ። ይህንን ሁሉ ሁኔታ በሕብረቱ አማካኝነት ለማረም እንዲቻል በሕብረት ኮሚቴው ላይ ሂስና ግለ ሂስ እንዲካሄድ ተወሰኖ ነበር ። ነገር ግን በነበረው አጣዳፊ የአገሪቱ ሁኔታ ስብሰባው አልተደረገም ።

ከግንቦት ወር 1969 ዓ.ም ጀምሮ መኢሶን በቀርብ ይመታል ለዚህም ደግሞ በአንዳንድ መ/ቤቶች በተለይም በመከላከያ ሚኒስቴርና በሕዝብ ደህንነት ውስጥ መኢ.ሶ.ንን የሚመቱ ቡድኖች ተቋቁመዋል ። የሚል መረጃ በየጊዜው ይደርሰን ጀመር ። በተጨማሪም በአንዳንድ ጓዶች ላይ ፀረ አብዮታውያን የወሰዱት እርምጃዎች ለምሳሌ ያህል የአቶ ጌታ አምበርበርና የጓድ አብዱላሂ መገደል እንዲሁም በአንዳንድ ክፍለ ሀገር በተለይም በሐረር ፤ በከፋ፤ በሸዋ አንዳንድ ካድሬዎች መታሰር በእርግጥ ወደ መኢሶን መመታት የሚያመራ መሰለ ። እነዚ በበኩሉ ለሊቀመንበሩና ለዋና ፀሐፊው የእኛ ጓዶች በየቦታ አስፈሪ ሁኔታ እንደገጠማቸውና መሥራት አለመቻላቸውን ደጋግሞ ገልጧል ነበር ። ምንም እንኳን ሊቀ መንበሩና ዋና ፀሐፊው ይህ የጥፋት ወሬ ነውና ጆሮአችሁን አትስጡት ቢሉንም በመኢሶን ውስጥ የተፈጠረው ሽብር መባባሱ ሊቆም አልቻለም ።

ስለዚህም ሦስት የመ.ኢ.ሶ.ን ጓዶች ማለትም := 1ኛ/ ዶክተር ከበደ መንገሻ ፤ 2ኛ/ ዳንኤል ታደሰ ፤ 3ኛ/ እኔ እራሴ የተሰየና ቀጠሮ ከሊቀመንበሩ ወስደን እቤታቸው ሄደን አነጋገርናቸው ። እሳቸውም በማብረታታት አይዟችሁ ግዴለም በማለት ሸኙተውናል ። ቢሆንም የመሸሸጉ "ታክቲካል ሪትሪት" ታምኖበት ስለነበረ በቁጥጥር ሥር ልናደርገው ባልቻልንበት ሁኔታ የወለጋ ክፍለ ሀገር ካድሬዎች መጥፋታቸውን ሰማን ። በዚህ ምክንያት

../..

የመሸሸጉ እርምጃ እንዲፋጠን ተደርጎ በዙያታችን ሸሸን ። ለዚሁ ሸሸት ምክንያቶች በመጽሔታችን በቁጥር 61 ላይ ተገልጿል ። በአጭሩ ለማጠቃለል ለሽሽቱ ምክንያት የሆነው ፡– 1ኛ/ መኢሶን ይመታል የሚለው ወሬ በመብዛቱ በጣም ተጋግሞ በመወራቱ ፣ 2ኛ/ በሕብረቱ ውስጥ በዚውን ጊዜ በድርጅታችን ላይ የጥርጣሬ እና ያለማመን ዝንባሌ በግልጽ ይታይ ስለነበረ ፣ 3ኛ/ በየክፍላተ ሀገሩና በአዲስ አበባም ጭምር በካድሬዎች ላይ የተወሰዱት – እርምጃዎች በእርግጥ የመኢሶንን መመታት የሚያሣይ ስለመሰለን ነው ። በተጨማሪም በአዲስ አበባ የተፈጠረው የቀልበሣ አደጋ ከፍተኛ መሆኑን እና በቻሣንሆን ሌሎችም ድርጅቶች አምነንበት ስለነበረ ይህም እንደ ተጨማሪ ምክንያት ሆኗል ። በተረፈ በመግለጫው ላይ እንደተገለጸው የመኢሶን አቋም ወይም መመሪያ ከሽሽቱም በኋላ ቢሆን አብዮታዊ ሂስ እንደሚሆንና መኢሶን በማንኛውም መንገዱ የመንግሥት ሥልጣን በአቋራጭ ለመያዝ የሚፈልግ አለመሆኑን ተናግሯል ።

በጥር ወር 1969 ዓ.ም ገደማ ከማሌሪደች ጋር ለመዋሃድ በሁለቱ ድርጅቶች ማለት በመኢሶንና በማሌሪድ መሐል ስምምነት ላይ ተደርሶ ነበር ። በዚሁ መሠረት በመጋቢት ወር ይመሰለኛል በተደረገው የድርጅታችን ኮንፈራንስ እንዲዛቱና በዚህ ኮንፈራንስ ላይ ውህደቱ እንዲጸድቅ ስምምነት ላይ ደርሰን ነበር ። በማይታወቅ ምክንያት ኮንፈራንሱ አንድ ቀን ሲቀረው እንሣተፍም አሉን ። በሚያዝያ ወር ይመስለኛል ውህደቱን ማስቀረታቸውን አስታወቁን ፣ በተለይ የሚያዝያ 23 በዓል አብረን ካዘጋጀን በኋላና ውጤቱ ደግሞ የሰደደ ጓዶችን እንዳስወደሰተ ሲገነዘቡ በመኢሶን ላይ ቀጥታ ዘመቻ ከፈቱ ። ግልጽ የሆነልን ነገር ማሌሪድና ሰደድ እንደተቆራረጡና በመኢሶን ላይ አንድ ዓይነት ግንባር እንደተፈጠረ ነበር ። ይህም ሁኔታ መኢሶን ይመታል የሚለውን ጥርጣሬአችንን አጠናከረው ፣ የጊዜያዊ ወታደራዊ መንግሥት ሊቀ መንበር ጓ መጀመሪያውን የእናት አገር ጥሪ ባደረጉበት ጊዜ መኢሶን ጥሪውን በሚገባ እንደሚደግፈውና አባሎቹ በያሉበት ሁሉ አብዮታዊት እናት አገር ወይም ሞት

በሚለው መፈክር ሥር ተሰልፈው ለመዋጋት ተዘጋጅተው ነበር ። በተለይም የ ሕዝባዊ ሠራዊት ምልመላ በተደረገበት ወቅት የእኛ ጓዶች ከተመልማዮች ጋር ታጠቁ ጦር ሠፈር ገብተዉ ለመሰልጠንና አብረዉ ለመዝመት ዝግጁነታቸውን ሲ ገልጹ ጦር ሠፈሩ እንዳይገቡና ተመልማዮች አስረክበው እንዲመለሱ ተገደዉ ዋል :: በተጨማሪም በሕዝብ ድርጅት ጉዳይ ጊዜአዊ ጽ/ቤት በኩል የመኢሶንም ሆነ የሌሎች ድርጅቶች ካድሬዎች በሕዝባዊ ሠራዊት ውስጥ ከላይ እስከ ታች በፖለቲካ ካድሬዎችና በመሪነት የሚገቡበትን መንገድ ለጊዜያዊ ወታደራዊ መንግሥት በጽሁፍ አስታወቀን ነበር :: ይሁንና በዚህ በካድሬዎች መሠማራት ጉዳይ ላይ በመንግሥት በኩል ብዙ ማመንታት ከታዬ በኋላ በመጨረሻ እንዲያ ውም የልዩ ልዩ ድርጅቶች በጦር ሠፈሩ ውስጥ መግባት ሠራዊቱን ሊከፋፍለው ይችላልና አይገቡበትም የሚል ውሣኔ የተወሰደ መሰለ :: በተጨማሪ እኔ ራሴ በግል ለሊቀ መንበሩ ባቀረብሁት የጽሁፍ ማስታወሻ ውስጥ ካድሬዎች ሠራዊቱን በድርጅት አንጻር እንዳይከፋፍሉ ራሱን የቻለ መመሪያ ሊወጣ እንደሚቻልና ከዚህ መመሪያውጭ ለመሥራት የሞከረ ካድሬ ሁሉ የሚሰናበትን እርምጃ ሊወሰድ በት የሚቻል መሆኑን ጠቁሜ ነበር :: ነገር ግን ሃሣቡ ተቀባይነትን አለማ ግኘቱ ግልጽ በሆነ መንገድ መኢሶንን ከአብዮታዊ ትግሉ የማግለል አዝማሚያ ሆኖ ታይቶናል :: ይህ እያታወቀ በሕብረቱ ድርጅቶች አካባቢ መኢሶን በጦር ነቱ ለመሣተፍ አይፈለግም የሚል ዘመቻ ተካሄደብናል :: ስለዘመቻው ጉዳይ የነበረንን አስተሣሰብና ፍላጐት በጽሁፍ በየወቅቱ ለጊዜአዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ አቀርበን ስለነበር እነሱን መመልከቱ አስፈላጊ ይመስለኛል ::

የሕዝብ ድርጅት ጉዳይ ጊዜአዊ ጽ/ቤትን መኢሶን በሞኖፖል ይዞታል የሚለው ቀረታ ለመጀመሪያ ጊዜ የተሰነዘረው በሰኔ 1968 ዓ.ም ነበር :: ከዚያ ጊዜ ጀምሮ በበኩላችን የጽ/ቤቱ መዋቅር የሚለወጥበትን መንገድ ስንፈልግ ቆይተን በመጨረሻ በጥር ወር 1969 ዓ.ም የመጀመሪያው የሕብረት ስብሰባ ሲደረግ የነበረንን አስተሣሰብ ለማቅረብ ችለናል :: በጥር 28 ቀን 1969 ዓ.ም የሕብረቱ አባል ድርጅቶች በአቀረብነው መዋቅር ውስጥ የሕዝብ ድርጅት ጉዳይ ጊዜአዊ ጽ/ቤት ሙሉ በሙሉ በሕብረቱ ቁጥጥር ሥር እንዲሆን ጠቁመን ይኸው ተቀባይነትን አግኝቶ አዋጁ ወጥቶ ለሥራ ተከናውኗል ::

ይህንን፣ የመዋቅር ለውጥ ሃሳብ ያቀረበው መኢሶን እንደሆነ እየታወቀ ከ
ሕብረት አባል ድርጅቶች መኢሶን ለውጡን አለተቀበለውም የሚል ስሜት ቀስቀስ
~~ዋል~~፣ እንዲያውም አንዳንድ ሰዎች የመኢሶን ሕብረቱ መግባት ምክንያቱ ይ
ኸው ነው እስከማለት ደርሰዋል ። ስለዚህ ጽ/ቤቱ ጉዳይና ስለተራማጆች
ሕብረት የሕብረቱን ስብሰባዎች ቃለ ጉባዔ መመልከትና መመርመር ያስፈልጋል ።

የኤርትራን ጥያቄ በሚመለከተው በኩል የመኢሶን አቋም በየካቲት 67
ዓ.ም በሰፊው ሕዝብ ድምጽ ቁጥር 22 ይመስለኛል በሠፊው ተዘርዝሯል ።
አቋማችን እንደተዘረዘረው የኤርትራ ተገንጣይ ድርጅቶች በኤርትራና በኢትዮ
ጵያ መሐከል ምንም ዓይነት የታሪክም ሆነ የባህል እንዲሁም የቋንቋ ግንኙነት
የላቸውም የሚለውን ካጋለጠ በኋላ በተጨማሪ በኢትዮጵያ ውስጥ አብዮታዊ እ
ንቅስቃሴ በተነሣበት ወቅት እነዚህ ድርጅቶች የኤርትራን ችግር በመሣሪያ
ኃይል ለመፍታት መሞከራቸው ከዓለም ፀረ አብዮት ኃይሎች ጋር የሚያስለፉቸው
ሆኑን ያጋልጣል ። የችግሩን መፍትሔ በሚመለከት ረገድ መኢሶን ያቀረበው
ሃሳብ በሦስት ነጥቦች ይጠቃለላል ።

1ኛ/ በዚያን ጊዜ ያስታራቂነትን ሚና ይዞ በነበረው በፕሬዚዳ
ንት ኑሜሪ አማካኝነት ወይም በሌላ ዘዴ በተኩስ ማቆም
ስምምነት ላይ ማድረስ ።

2ኛ/ ሰፋ ያለ ውይይት ተከፍቶ ለሦስት ወይም ለአራት ዓመታት
ፍጹም የሆነ ሠላማዊ ሁኔታ እንዲኖር ማድረግ ፣ በነዚህ
የሰላም ዓመታት ውስጥ የኤርትራና የኢትዮጵያ ሕዝቦች ዲ
ሞክራሲያዊ የሆነ የበሰለ ጥያቄና የኤርትራን መገንጠል
የሚመለከት ሰፊ ውይይት እንዲያካሂዱ ማድረግ ።

3ኛ/ ከእነዚህ ዓመታት በኋላ የኤርትራ ሰፊ ሕዝብ ነፃ በሆነ
መንገድ የራሱን እድል እንዲወስን ማድረግ ።

እነዚህ መኢሶን ያቀረባቸው ሃሳቦች በጊዜው ተደማጭነትን አላገኙም
ሕዝብ ድርጅት ጉዳይ ጊዜያዊ ጽ/ቤት ከተቋቋመና የኢትዮጵያ ብሔራዊ ዲሞ

../..

ከራሲያዊ ፕሮግራም ከወጣ በኋላ በፕሮግራሙ ላይ በመመሥረት ጊዜያዊ ወታደራዊ መንግሥት ሚያዝያ 9 ቀን 1968 ዓ.ም በኤርትራ ከተገንጣይ ቡድኖች ጋር የውይይትን መንገድ የሚፈልግ አንድ ቡድን አቋቋመ ። ይህ ቡድን ኤርትራ እንደደረሰ በኢ.ፒ.ኤል.ኤፍ / / የመጀመሪያውን ደብዳቤ ጻፈ ። ይህም ድርጅት ለቡድኑ በጻፈው መልስ በመሠረቱ ለውይይት ዝግጁ መሆኑንና ነገር ግን ከዚያ በፊት የኢትዮጵያ መንግሥት ሦስት ነገሮችን እንዲያሟሉ ጠየቀ ።

1ኛ/ በኤርትራ ሁለት ድርጅት እንዳሉና ለውይይት ለሁለቱም ድርጅቶች ጥሪ መደረግ እንዳለበት ።

2ኛ/ ይህ ሂደት ረዥም ያለ ጊዜ የሚፈልግ መሆኑን የኢትዮጵያ መንግሥት እንዲያውቀው ።

3ኛ/ በዚያን ጊዜ በዘገዶት ላይ የነበረው የራዛ ዘመቻ እንዲቀር ።

እነዚህን ነጥቦች ይዞ ቡድኑ ለጊዜያዊ ወታደራዊ መንግሥት ካቀረበ በኋላ ግንቦት 8 ቀን 1968 ዓ.ም የኤርትራን ችግር በሰላማዊ መንገድ ለመፍታት ባለዘጠኝ ነጥብ የፖሊሲ ውሳኔ ወጣ ። ይህንን ውሳኔ መሠረት በማድረግ ቡድኑ ከድርጅቶቹ ጋር መጻጻፍን ቀጠለ ። በነሐሴ 1968 ዓ.ም ኢ.ፒ.ኤል.ኤፍ / / ለሁለቱም ድርጅቶች የኢትዮጵያ መንግሥት በታና ጊዜ ወስኖ ያስታውቅ ፤ ኢ.ኤል.ኤፍ ከመጣ መጣ እኛ ግን አንቀርም የሚል መልዕክት አስተላለፉ ። ይኸው ጉዳይ ለጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ ቀርቦ ኢ.ፒ.ኤል.ኤፍ በዚህ መልዕክቱ ላይ ማብራሪያ እንዲሰጥ እንዲጠየቅ ተወሰነ ። ቡድኑም ለመጨረሻ ጊዜ ለኢ.ፒ.ኤል.ኤፍ ማብራሪያ የሚጠይቅ ደብዳቤ ጽፎ ወደ አዲስ አበባ ተመለሰ ። በመስከረምና በጥቅምት 1969 ዓ.ም አካባቢ በአዲስ አበባ በደርግ ውስጥና ከዚያም በኢ.ሕ.አ.ፓ በከተማ ውስጥ በተፈጠረው ሁኔታ ምክንያት የውይይት ቡድኑ ምንም ዓይነት ግልጽ ውሳኔ ሳያገኝ ሥራውን አቋረጠ ። በተጨማሪም በሐምሌ ወር 1968 ዓ.ም የግንቦት 8ን የፖሊሲ ውሳኔ ከሥራ ላይ ለማዋል ያወጣው የአጭር ጊዜ መመሪያ ከሥራ ላይ ሳይውል ቀረ ። በአጭር ለማስታወስ የምፈልገው

የግንቦት 8 የፖሊሲ ውሣኔ መውጣቱና የኤርትራ ልዩ ኮሚሽን መቋቋሙ በእርግጥ ትክክለኛ እርምጃዎች መሆናቸው ሲታወቅ በፖለቲካ በኩል ግን የማያቋርጥ ጥረት ተደርጓል ለማለት አያስደፍርም ። የእኔ እምነት በአሁኑ ሁኔታም ቢሆን ከነዚህ ተገንጣይ ድርጅቶች ጋር እንደምንም ተቀብሎ የውይይት መድረክ ካልተከፈተ በስተቀር የኤርትራን ችግር በቀላሉ ለመፍታት ይቻላል የሚል እምነት የለኝም ። የኢትዮጵያ መንግሥት ለሁለቱ ድርጅቶች ፀረ አብዮተኛነታቸው እያወቀም ቢሆን ፣ ጥሪ ቢያደርግላቸው በፖለቲካ በኩል የሚጎዳው ነገር የለም እንዲያውም የዚህ ዓይነት እርምጃ የኤርትራን ሠፊ ሕዝብ ድጋፍ ለማግኘትና የማይቀረውን የድርጅቶች የእርስ በርስ መጣላት ሊያፋጥን ይችላል ።

በሠፊው ሕዝብ ድምጽ ቁጥር 61፣ ላይ በጠቀሰው በፖለቲካ ፣ በኢኮኖሚና በማሕበራዊ ኑሮ በኩል በአገሪቷና በአብዮቱ ላይ ከፍተኛ ውጥረት እንደደረሰ የተጠቀሰበት ምክንያት ሠፊው ሕዝብ እነዚህ ችግሮች እንዳሉ እንዲያውቁና እንዲቋቋማቸው እንዲሁም መንግሥት በበኩሉ ተገቢ የሆኑትን እርምጃዎች እንዲወስድ ለመገፋፋት ነው ። በተረፈም ጸሁፉ ለእነዚህ ውጥረቶች መፍትሔ ይሆናሉ ብሎ የገመታቸውን እርምጃዎች በመጨረሻው ላይ አስፍሯል ።

ከዚህ በላይ በጠቀስኳቸው ምክንያቶች አጭር በጣም ፍርጠት ስለአደረብን ታክቲካል ሪትሪት ማድረግ አለብን በማለቱ በመጋቢት ወር 1969 ዓ.ም ይመስለኛል ኮንፈራንስ ባደረግን ጊዜ የታወቁ የመኢሶን አባሎች መሸሸግ እንደሚያስፈልግ ተወሰነ ። በዚህ መሠረት ዝግጅት ተደርጎበት ቢታ እስኪገኝ ድረስ የተሻሉ መረጃዎች ማለት መኢሶን ይመታል ስለሚለው ሁኔታ ለማግኘት ሙከራ ተደረገ ። ይሁንና የተገኙት መረጃዎች በሙሉ ይህንኑ የሚያጠናክሩ በመሆናቸው ሪትሪት / መሸሸጉ/ እንዲከናወን በነሐሴ ወር መጀመሪያ ላይ ተወሰነ ። በዚህ መሠረት ነሐሴ 14 ቀን 1969 ዓ.ም ቀዳሜ በግምት ከጧቱ አራት ሰዓት ተኩል ላይ በእንዲት የሕዝብ ድርጅት ጉዳይ ጽ/ቤት ኮምቢ ቮክስዋገን መኪና := 1ኛ/ እኔ ራሴ ፣ 2ኛ/ ዶ/ ከበደ መንገሻ ፣ 3ኛ/ ምትኩ ተርፋሣ፣ 4ኛ/ አቶ አዳኝ የአባቱን ስም የማላውቀው፣

../..

5ኛ/ ሽፈራቸን የነበረው ዳንኤል የአባቱን ስም የማላውቀው ፣ 6ኛ/ አንድ ስሙን የማላስታውሰው ሰው ሆነን በጎጃም መንገድ ወጣን ። ከጨከጮ በታች ሰንደር ከመኪናው ወርደን አብሮት ከነበረው ገበሬ አቶ አዳኝ ጋር በእግር ወደዚሁ ሰው ቤት ሄድን ። እስከ ሐሙስ ነሐሴ 19 ቀን 1969 ዓ.ም ድረስ ከዚሁ ገበሬ ቤት ቆየን ። ከሄድነው ውስጥ ና ቀደመውን እዚሁ ሰው ቤት ከነበረት አራት ሰዎች በየገበሬዎቹ ቤት መከፋፈል ስለነበረብን ፣ ሦስታችን ማለትም ፣ 1ኛ/ እኔ ራሴ ፣ 2ኛ/ አበበ ኃይሌ፣ 3ኛ/ አያሌው ወልዴ መዱህን ነሐሴ19 ቀን 69 ዓ.ም አቶ ሁኔዬ ከተባለው ገበሬ ቤት ተዛወርን ። እዚህ ቤት እስከ ቅዳሜ ነሐሴ 28 ቀን 1969 ዓ.ም ድረስ ቆይተን በዚሁ ዕለት ማለት ከምሽቱ አምስት ሰዓት ላይ ሌላ ገበሬ ቤት የነበሩትን ሁለት ጓዶች ማለትም 1ኛ/ የራስወርቅ አደማሴ ፣ 2ኛ/ ደረጀ ዓለማየሁ ፣ እና ዘንዱ መጡ ። ከአዲስ አበባ ወታደሮች እንደመጡ በማግስቱ አሰሣ እንደሚደረግ ነገሩን ። ከተመካከርን በኋላ አምስታችን ሌሎቹ ጓዶች ይገኙበታል ወደተባለው ወደ አቶ መገርሣ ቤት ተጓዝን ከሌሊቱ 8 ሰዓት ተኩል ላይ ደረስን ፣ እዚያም ስንደርስ ቀደመው ሄደዋል ተባልን ። እነ አቶ መገርሣን መንገዱ ምሩን ብንላቸው ፈቃደኞች ስላልሆኑ ብቻችንን ዝም ብለን አንዱ አቅጣጫ ወሰደን ወደ ሙገር ወንዝ ያደርስናል በምንለው አቅጣጫ ተጓዝን ። እሁድ ነሐሴ 29 ቀን 1969 ዓ.ም ጫካ ውስጥ ተቀምጠን ዋልን ። በዚሁ ቀን በዘጠኝ ሰዓት ገደማ የእኛ ጓዶች ይገኙበታል በተባለበት አካባቢ ኃይለኛ የአውቶማቲክ ተኩስ ሰማን ። በዚህ ሁኔታ የእኛ ጓዶች ተገድለዋል የሚል ግምት አደረብን ። ምን ማድረግ አለብን ብለን ስንመካከር ሁለት ምርጫዎች ቀረቡ፡= 1ኛ/ ወንዙን ተከትለን ወደ ሙገር ሸለቆ መግባት፣2ኛ/ እንደምንም ከበባውን በጥስ አዲስ አበባ መድረስ ነበር ። በዚህ ላይ ከተወያየን በኋላ ሁለተኛው ምርጫ ተወሰደ ፣ እሁድ ማታ ከአንድ ሰዓት ገደማ ጫካው ወጣን የአዲስ አበባን መንገዱ እናገኛለን ብለን ባሰብነው አቅጣጫ ገሰገስን ። አስር ሰዓት ተኩል ያህል ከተጓዝን በኋላ አንድ ተራራ ዘንድ

ደርሰን ጫካ ውስጥ ገብተን ተቀምጠን ዋልን ። ሰኞ ዕለት ነሐሴ 30 ቀን 1969 ዓ.ም ማታ በአንድ ሰዓት ገደማ የያዝናቸውን አራት አውቶማቲክ መሣሪያዎቻችንና ጥይቶቻቸውን ካርታዎችን እዚያው አምባው ውስጥ ሸጠናቸው እንደገና ጉዞ ቀጠልን ። ከለሊቱ ሰባት ሰዓት ተኩል ላይ ከአንድ ከማናውቀው ገበሬ ቤት ሄደን የሚበላ ነገር እንዲሰጡን ጠየቅን ። ቆሎ ቆልተው ከሰጡንና ውሃ ካጠጡን በኋላ መንገድ እንዲያሣዩን ጠይቀናቸው መንገድ አሣይተውን ጉዟችንን ቀጠልን ። ማክሰኞ ጳጉሜ 1 ቀን 1969 ዓ.ም ከጧዋቱ አስራ ሁለት ሰዓት ተኩል ላይ የመኪና መንገዱ አገኘን እስከ ሦስት ሰዓት ድረስ ተጉዘን ከጫንጮ ወዲህ አንድ እርሻ ቤት ደረስን እዚያ ሆነን መኪና መጠበቅ ጀመርን ። ነገር ግን ጫንጮ የገበያ ቀን ስለነበረ መኪና ለማግኘት ስላልቻልን የመኪናውን መንገድ ተከትለን ወደ ሱሉልታ ተጓዝን ። ሱሉልታ ልንደርስ በግምት አምስት ኪሎ ሜትር ሲቀረን አንድ ፍርድ ታኖስ የዕቃ መጫኛ ዓይነት መኪና አገኘንና ሱሉልታ እንዲያደርሰን ጠየቅነው ። እሱም አሣፍሮን ከሱሉልታ አሣልፎን አንድ የደር አርባታ ከሚባል እንዲያወርደን ጠይቀነው ነበር ግን አሣልፎን የቀበሌ ማኅበር አባላት ካሉበትና ሕዝብ ከተሰበሰበበት አካባቢ አወረደን ። ከዚያም የቀበሌ ማኅበር አባላትና ሕዝቡ ከበበንና ፍተሻ ሲያደርጉብን ሽጉጦችና መታወቂያ ወረቀቶቻችንን አገኙብንና ኬላው ላይ ወደሚጠበቁ ወታደሮች ዘንድ ወሰዱን ከዚያም ከ3ኛ መምሪያ ዎታ ዘዙ መኪናዎች መጥተው ይዘውን አመጡን ። አዲስ አበባ ለመመለስ ያሰብነው እዚህ መጥተን ለመሸሸግ ነበር ። በፊት ግን የታቀደው 15 ቀን ያህል ሙሉ ቆይተን ከዚያ መንገድ በሚያውቁ ሰዎች እየተመራን በጎንደርደረት በኩል ወሎ ጋ ለመግባት ነበር ። ነገር ግን ሣይሣካልን የአሰሣው ነገር በድንገት መጥቶብን ልንያዝ በቃን ።

" ...ከአዲስ አበባ ልንሸሸግ በወጣን ጊዜ የያዝነው እኔ በበኩሌ አንድ ዑዚ ከ32 ጥይትና አንድ ካርታ ብቻ ነበረኝ ፤ እዚያ ከደረስን በኋላ እንደገና የመሣሪያ ክፍፍል ተደርጎ አንድ ክላሺን ከ90 ጥይት ጋር ደርሶኝ

እንዲነስ እንደመኢሶን፣ ያለው ለጋ ድርጅት ይቀርና የረዥም ጊዜ ልምድ ያላቸው ኮሚኒስት ፓርቲዎች ለምሳሌ የግሪክ የሱዳን የኢንዶኔዚያ ኮሚኒስት ፓርቲዎች የፓለቲካ ስህተቶችን በማድረጋቸው ከፍተኛ ውድቀት ደርሶባቸዋል :: ምናልባት የመኢሶንን ሁኔታ ከእነዚህ ፓርቲዎች የሚለየው እነሱ በፋሽስታዊ ጭንታዎች እጅ ሰወድቁ መኢሶን ግን በማርክሲዝም ሌኒንዝም በሚያምኑ መንግ ሥት እጅ ወድቋል :: ስለዚህም በእኔ ግምት ከእነዚያ የተሻለ ዕድል ያገኛ መዋል ቢፈ እምናለሁ ::በተረፈ ግን የኢትዮጵያን አብዮት በሚመለከት በኩል በሌ ሌጅ ጥያቄዎች ላይ መኢሶን የወሰዳቸው አቋሞች ትክክለኛ ናቸው ብዬ አምናለሁ :: ይህ ከዚህ በላይ የተመዘገበው ትክክለኛ ቃሌ ለመሆኑ አንብቤ ፈረምኩ ::

<u>ተጨማሪ ቃል :=</u>

ከዚህ በፊት በሰጠሁት ቃል ላይ ዛሬ መስከረም 5 ቀን 1969 ዓ.ም የምሰጠው ተጨማሪ ቃል ሚያዝያ 23 ቀን 1969 ዓ.ም የተከበረው የወዝ አደር በዓል በኋላ አንዳንድ የሸደዱ ጓዶች ናቸው ብለን የምና ስባቸው ሰዎች ለምሳሌ ሲኒየር ቴክኒሻያን ደምሰው በሕዝብ ስብሰባዎቸ መኢሶን ሉሳው ኢ.ሕ.አ.ፓ ነው :: በቅርቡ ይመታል ብለው እስከመናገር ደ ርሰዋል ::እንደዚሁም የጓድ አለቃ ለገሠ ፒያ ታምራት ፣ መ/አለቃ ዱንቁ.ይ ህንኑ ሐሣብ ደጋግመው ለእኔና ለጓደኞቼ በማስፈራሪያ መልክ ገልጸውልናል :: በተጨማሪ ሻለቃ እንዳሉ የደርግ የቋሚ ኮሚቴ አባል የሆኑት መኢሶን ነሐሴ 15 ቀን 1969 ዓ.ም ያልቀለታል ሲሉ ለግብጽ አምባሣደር መግለጫ ለመስ ጠታቸው ኢንፎርሚሽን ደርሶናል :: ከነዚህ ሰዎች መካከል ለምሳሌ የጓድ አለቃ ለገሠ፣ ፒያ ታምራትን በምናነጋግርበት ወቅት በእርግጥ ሚያዝያ 23 ቀን

../..

ከተደረገው ሰልፍ በኋላ ለንግታ ምንም ያህል አልቀረንም በለውናል ፣ ስለዚህም ጉዳይ ለመነጋገር በሕብረቱ ሂስና ግለ ሂስ ይካሄዳል ተብሎ ነበር አልተካሄደም ይህ ሁኔታ ስላስፈራን ጊዜው እስከሚያልፍ ድረስ በአንደር ግራውንድ ውስጥ ገብተን ለመስራትና ለመሰወር ወሰንን ፣ በተለይ አንደር ግራውንድ ለመግባት ያስፈለገን የዲሞክራሲ መብቶች እስኪሟሉልን ድረስ ሲሆን ከዚያም ተመልሰን በግልጽ ለመስራት ብቻ ነው ። ዝርዝር መግለጫም የሰፊው ሕዝብ ድምጽ ቁጥር 61 ላይ ገልጸነዋል ። ሲግ ወታደሮችን መልምሎ አሰልጥኗል በጽሁፍ ላይ ያሰፈርኩት በግምት እንጂ በቂ መረጃ የለኝም ፣ በጽሁፉ ማለትም የሕዝብ ድርጅት ጉዳይ ጽ/ቤትና መኢሶን በሚለው አትም ላይ ያወጣሁት ለሂስና ለግለ ሂስ መንደርደሪያ ይሆናል ብዬ ነው ። በዚሁም መሠረት ለሕብረት አባሎች ወረቀቱን ሰጥቻለሁ ። የድርጅት ደረጃ ከደርግ ው ስጥ የመለመልነውም ሆነ የተለየ ግንኙነት የለኝም ። በሥራ ምክንያት ከምአውቃቸው በስተቀር የተለየ ነገር የለኝም ። ሻምበል በፍቃዱ የሰፊው ሕዝብ ድምጽን ከሚያነብና ከሚያሰራጭ በስተቀር የመኢሶን አባል አይደለም ። እሱ የጻፈውን ወረቀት ሊገኘው የቻልኩት በዶክቶር ከበደ መንገሻ በኩል ነው ። በሁለቱ መሐከል ያለውን ግንኙነት አላውቅም ፣ ከሻምበሉ ጋር እኔም ከሠፈምታ በስተቀር ጠለቅ ያለ ግንኙነት የለኝም ። ወረቀቱንም የጻፈው ለወታደራዊ ፓለቲካ መምሪያ ሲሆን እኛም ካየነው በኋላ ከሻምበሉ ጋር ያለን ግንኙነት ያው እንደበፊቱ ነበር ። የሰጠነውም ምክር የለም ። ስለ እስኳድ መቋቋም ጉዳይ በበኩሌ የማውቀው ነገር የለም፣ መቋቋሙንም አልሰማሁም ፓለቲካ ት/ቤት ውስጥ ስለማደሩ ጉዳይ አንዱ የማውቀው ነገር በጥቅምትና በሕዳር ወር 1969 ዓ.ም የኢ.ሕ.አ.ፓ ግድያ በተፋፋመበት ወቅት 3 ሌሊት ያህል ፡= 1ኛ/ አቶ አንዳርጋቸው አሰግድ ፣ 2ኛ/ ዶክተር ነገደ ጎበዜ ጋር አብሬ አድሬአለሁ ፡፡ ለእስኳዱ አስለጣኝ መለዮ ለባሽ መኖሩንም አልሰማሁም ፣ አላውቅም ። ስለ ሕብረት ያለን አቋም በመግለጫችን ውስጥ በደንብ ተጠራርቶአል፣ በሕብረቱ ላይ ያለን ሂስ ሕብረቱ በእኩልነት በደንብ

../..

ያልተመሰረተ በመሆኑና በተለይም ከሰፊው ሕዝብ በስተጀርባ በመሰራቱና የቤተ መንግሥት ዱለታ በመምሰሉ ነው ። ስለዚህም የተራማጆችን ሕብረት እንመስርት ስንል በጽሁፍ ውስጥ እንደተገለጸው ሁሉ ዲሞክራሲያዊ መብቶች ኖረው በይፋና በጠቅ በሰፊው ሕዝብ ፊት ሕብረታችንን እንመስርት ለማለት ነው ።

እኔ እስከማውቀው ድረስ / ከአባል/ መስራች አባሎች አሁንም በ ድርጅቱ ውስጥ ያለነው 1ኛ/ እኔ ራሴ ፣ 2ኛ/ አቶ አንዳርጋቸው አሰግድ፣ 3ኛ/ ዶክተር ነገደ ጎበዜ ፣ 4ኛ/ ዶክተር ከድር መሐመድ ፣ 5ኛ/ ዶክተር ወርቁ ፈረደ ፣ 6ኛ/ አቶ ሲሣይ ታከለ ናቸው ። የቀሩት በአሁኑ ሰዓት አቋማቸው ምን እንደሆነ አላውቅም ፣ እነዚህ መስራች አባሎች የነበሩት እኔ እስከማውቀው ድረስ ምንም የአደረጉት አስተዋጽኦ የለም ። በአመራር ውስጥ በነበርነው ሰዎች መካከል ምንም ዓይነት የአቋም ቅራኔ አልነበረም ። የአ ምም፣ ከአመራር ውጭ በነበሩት ግን ሊኖር እንደሚችል ለሁሉም ግልጽ ነው ። "ቀይ ፋና" የሚባለውን መጽሔት እኔ የአነበብኩት አንድ ቁጥር ብቻ ነው ። ስለ ዚህም ለጊዜው ቁጥሩ ተከታትሎ እስከሚወጣና አስተሳሰቡ ግልጽ የሆነ አቋሙን እስኪይዝ ድረስ በዚች አንድ ቁጥር ላይ አስተያየቴን መስጠቱ ሚዛናዊ አይመስለኝም ። ስለ የሰጠሁትን ተጨማሪ ቃል አንብቤ ፈረምኩኝ ።

ከላይ እንደገለጽኩት ሕብረቱ የቤተ መንግሥት ዱለታ ይመስላል ያ ልኩት የቤተ መንግሥት ዱለታ የሚለው ከእንግሊዘኛው ፓላስ ኢንትሪግ / / የሚለው ለመተርጐም የተወሰደ ሲሆን ይህም ማለት በጥቂት ግለሰቦች መካከል ብቻ የሚደረግ ውይይትና ስምምነት እንጂ ባደባባይ በሰፊው ሕዝብ ፊት ክርክር የማይደረግበት ነገር ማለት ነው ። ሕብረቱ ያ ካሄዳቸው ስብሰባዎች አጀንዳቸውም ሆነ የውይይቶቹ ይዘት እንደዚሁም እያን ዳንዱ ድርጅት በልዩ ልዩ ጥያቄዎች ላይ የወሰዳቸው አቋሞች ሌላው ቢቀር በየድርጅቱ ለሚገኙ እንኳን ወጥተው ውይይት የማይካሄድባቸው ስለነበሩ በእር ግጥም የቤተ መንግሥት ዱለታ ይመስላሉ ። ለምሳሌ ስለ ዲሞክራሲያዊ መብቶች

ወ.ዘ.ተ..እያንዳንዱ ድርጅት የወሰዳቸው እቃዎች በዩፉ ተገለጸው ለሰፊው ሕዝብ ውይይት አለቀረበም ፣ በዚህ በኩል ለምሣሌ የደበበ የመንን 3 ፓርቲዎች ምሣሌ በንወስዱ ሕብረትን ለመፍጠር ያቻሉት ለሦስቱም ፓርቲዎች ነፃ የሆነና አኩል መድረክ ተከፍቶላቸው በሬዲዮ በጋዜጣም በሰፊው ሕዝብ ፊት ግልጽ የሆነ ውይይትን ካካሄዱ በኋላ ነበር ። የኢትዮጵያን ማርክሲስት ሌኒኒስት ድርጅቶች በማመለከተው በኩል ግን እንኳንስ የዚህ ዓይነቱ ዲሞክራሲያዊ ሁኔታ ሊፈጠርላቸው ቀርቶ ድርጅቶቹ ሕጋዊ ሰውነት እንኳ የላቸውም ፡፡ ይህም ሕብረቱን ላይ እንደተባለው የቤተ መንግሥት ዱለታ ያስመስለዋል ።

<u>ተጠሪ ቃል የቀጠሉ ።</u>

ከዚህ በፊት በሰጠሁት ቃል ላይ ዛሬም መስከረም 6 ቀን 1969 ዓ.ም ከቀኑ 9 ሰዓት ሲሆን በደርግ ምርመራ ክፍል ቀርቤ የምሰጠው ተጨማሪ ቃል ፡= ከቤታችን ውስጥ በፍተሻ ከተገኙት ዳኩሜንቶች ውስጥ አንዳንዱ የኩድ ስሞች አሉ እነሱም ፡=

| <u>የኩድ ስም ፡=</u> | <u>ደንበኛ ስም ፡=</u> |
|---|---|
| ገበየሁ | አቶ ዳንኤል ታደሰ |
| ወልዴ | ,, አንዳርጋቸው አሰግድ |
| ግዛው | ,, ብርሃኑ / አርሸ ሚ. የሚሰራ/ |
| መላኩ | ,, ኃይሉ ፊዳ |
| ሚካኤል | ዶክተር ተረፈ ወ/ ጻዲቅ |
| ነጋ | ,, ከበደ መንገሻ |
| ነጋልኝ | ,, ነገደ ጎበዜ |
| አሰረግደው | አቶ መስፍን ካሱ |
| አሸናፊ | ,, ሲሣይ ታከለ |
| አይዳ | ዶክተር ንግስት አዳነ |
| ጉግሣ | አቶ ታደሰ ገሠሠ ናቸው ። |

../..

ሐምሌ 12 ቀን 1969 ዓ.ም በግምት ከምሽቱ አንድ ሰዓት ጀምሮ ምናልባት በእኔ ቤት በተደረገው ስብሰባ ፡= 1ኛ/ እኔ እራሴ ፤ 2ኛ/ አቶ መስፍን ካሱ ፤ 3ኛ/ ዶክተር ከበደ መንገሻ ፤ 4ኛ/ አቶ ዳንኤል ታደሰ ፤ 5ኛ/ አቶ ሲሣይ ታከለ ሆነን በተደረገው ስብሰባ ላይ ከሚሊሽያው አዛዦች ዉስጥ አንዳንዶቹ የመኢሶን መስመር የሚከተሉና በአሁኑ ጊዜ ምን እናድርግ በማለት ከመኢሶን አመራር ሃሣብ የጠየቁ መኖራቸውን አቶ መስፍን ካሱ ገለጸልን ፤ የሰዎቹም ስም ፡= 1ኛ/ ኮ/ ደሣለኝ የ5ኛ ሚሊሽያ ክፍለ ጦር የአንደኛ ብርጌድ አዛዥ ፤ 2ኛ/ ሻለቃ ጉሹ ወልዴ ፤ 3ኛ/ ቱሉ የሚባል ማዕረጉንና የአባቱን ስም የማላውቀው ለመሆናቸው ዝርዝር ገለጸልን ፡፡ የእነዚህ ሰዎች ስምና ሁኔታ የተገለጸው አቶ መስፍን ካሱ ነው እኔ እስከ ማውቀው ድረስ በተራ ቁጥር 2 እና 3 የተጠቀሱት በሌላ ምክንያት የተጠቀሱ ናቸው ማለትም ደጋፊዎች ይሆናሉ ማለቴ ነው ፡፡ ደግሞ ከእኔ ያበለጠ የስብሰባውን ቮርቫል የጻፈው አቶ ሲሣይ ታደሰ ያውቅ ይሆናል ፡፡

በዚሁ /ስብሰባ/ ልዩ ስብሰባ ላይ በወታደራዊ ካድሬዎችና ከላይ በተጠቀሱት ሰዎች መካከል ቅራኔ አለ ሲሉ መስፍን ሃሣቡን ከሰነዘረ በኋላ አቶ ዳንኤል አዛዦቹ ከካድሬዎቹ በፓለቲካ፣ ንቃት ምን ያህል ይሻላሉ የሚል ጥያቄ አቀረበ ፡፡ ከዚያም መስፍን ምናልባት በንቃት ምንም ያህል ላይበላለጡ ይችላሉ የሚል መልስ የሰጠ ይመስለኛል ፡፡ ዶክተር ከበደም መጀመሪያ እነዚሁ ሰዎች ጁንታን ሊያቋቁሙ ይችላሉ ወይንም ደግሞ በነኰሎኔል መንግሥቱ የተጠመደልን ወጥመድ ሊሆን ይችላል ፤ የሚል ሃሣብ አቀረበ ፤ ቀጥሎም እኔ " ኮ " አይጠቅምም ሰዎችን እናውቃቸውም ቲፓቸውን በደንብ እናውቅም ፤ ስለዚህ በየሄዱበት ጠሩንና ሕዝቡን ለማቀሃዱ ይመክሩ ስል ሃሣቤን ሰጠሁ ይህንንም ያልኩት አንደኛ ሰዎቹ በፓለቲካ ያላቸው ንቃት ይህንንም ያህል አለመሆኑ ስለተገለጸልን ከሁሉ አስቀድሞ የሚታያቸው ነገር ሙፈንቅለ መንግሥት መሆኑን በመገንዘብ እና መኢሶን ደግሞ በዚህ ዓይነቱ አሰራር የማያምን መሆኑን ስለማውቅ ፤ 2ኛ/ ከላይ ዶክተር ከበደ እንዳለው ሁሉ ሰዎቹን ስለማናውቃቸው በእርግጥም ነገሩ ወጥመድ መሆን ስለሚችል ለእብ ጽቶ

../..

በእግርጥ መሥራት ከፈለጉ በየሄዱበት ሁሉ በሕዝብና በሠራዊቱ መጠከል አንድነትን ያመስርቱ በማለት ነበር ፤ ነገር ግን ምቲኛቸውና ሰዎች በደንብ ቢታወቅ ኖሮ := 1ኛ/ በሠራዊቱ ውስጥ በተደራጀ መንገድ የመኢሶንን ሶሻሊቲካ መስመር እንዲያስፋፉ ፤ 2ኛ/ ከላይ እንደተባለው ሁሉ በሰፊው ሕዝብና በሠራዊቱ መጠከል የጠበቀ ወዳጅነት እንዲመሰርቱና በዚህም የአብዮታዊ ጦር ጠባዩን እንዲቀዳጅ እና 3ኛም ለረጅም ጊዜ ለሕዝባዊ አብዮታዊ ጦርነት እንዲዘጋጅ ለመምከር ነበር :: ከዚያም በተከታይ አቶ ዳንኤል አዚህ "ኩ·" ቢያደርጉ ኤርትራ ትገነጠላለች ስለ ኤርትራ ምንድነው አቋማቸው ኤርትራ ውስጥ አስተማማኝ ኃይል አላቸው ወይ ፣ የሚል ጥያቄ ለሰብሰባው ቀረበ ፤ ለዚህም መልሱን የሰጠው ሰው ማን እንደሆን ለጊዜው ትዝ ባይለኝ የመልሱ ስሜት እነዚህ ሰዎች መንግሥትን ለመገልበጥ ተነስተው ከሆነ እኛ ምንም ለማድረግ እንደማንችል የተገለጸ ይመስለኛል :: በመጨረሻም ከላይ ስለተጠቀሱት ነጥቦች ሰብሰባው በዝርዝር ከተነጋገረባቸው በኋላ የሚከተለውን ውሣኔዎች አስተላልፍአል ::

ይኸውም ከላይ የተጠቀሱት ሰዎች :=

1ኛ/ በጦሩ ውስጥ የፖለቲካ ሥራ እንዲሰሩ

2ኛ/ የሰደዱን ሰዎች ገለልተኛ / / እንዲያደርጉ ::

3ኛ/ ፒዛንት ካድሬዎች ውስጥ ደህና ሰዎች ስላሉ እንዲይዟቸው አጋዦች መሳክ እንደሚቻል ::

4ኛ/ ስለ ሚልሽያው አመዳደብና ይዘት/ /
እንዲነግሯቸው ና ቸው :: ~~ከለ ቃሉን ሰጥቼ ፈርሜአለሁ ::~~

<u>ባለፈው የቀጠለ ተጨማሪ ቃል :=</u>

ጥምሌ 13 ቀን 1969 ዓ.ም በግምት ከምሽቱ አንድ ሰዓት ጀምሮ በአኔ ቤት ይመስለኛል በዚህ ሰብሰባ የተገኘኙ ሰዎች :=

…/..

1ኛ/ አቶ መስፍን ካሱ
2ኛ/ ዶክተር ነገደ ጎበዜ
3ኛ/ አቶ ዳንኤል ታደሰ
4ኛ/ ዶክተር ከበደ መንገሻ
5ኛ/ አቶ ተረፈ ወ/ጻዲቅ
6ኛ/ ,, አንዳርጋቸው አሰግድ
7ኛ/ እኔ እራሴ /አቶ ኃይሌ ፊዳ/
8ኛ/ አቶ ሲሣይ ታከሎ ሆነን

ተሰብስበን በዚህ ቀን የነበረን አጀንዳ ስለ ሕብረቱ ፣ ስለ ሕዝብ ድርጅት ጉዳይ ጽ/ቤት እና ስለ ፓለቲካ ት/ቤት ስምችን ማለትም ከመኢሶንም ድርጅት ተካፋዩ የነበሩትን ለመመደብ ነበር ። በስብሰባው መጀመሪያ ላይ ዜና መለዋወጥ ስለነበር በዚያን ሰሞን እነ ሌ/ኮ/ መንግሥቱ ኃ/ ማርያም አግኝቼ ስነበር ፣ እሣቸው የጠየቁኝንና የነገሩኝን አንዳንድ ነገሮች ለስብሰባው ሪፖርት በማድረግ ስብሰባው ተከፈተ ። እነዚህም ነገሮች የሚከተሉት ናቸው ።

1ኛ/ መኢሶን ከሠራተኞች ነብረት ጋር እንዲቀራረብ ቀስቃሽ ሲያደርግ ቆይቶ አሁን ግን ለምን ስለ ሰሻል ኢምፔር ያለዝም ያነሣል?

2ኛ/ ሕቡዕ ለምን አንገባለን ትላላችሁ ?

3ኛ/ ወታደሩ ውስጥ የፓለቲካ ሥራ ለምን አንሰራለን ትላላችሁ ?

4ኛ/ ስደዱ ቢሮክራሲያውን ይመለምላል ትላላችሁ ?

በእውነቱ ግን ቢሮክራሲውን የያዛችሁት መኢሶንና ኢጭአትና ናችሁ ። ደግሞም ኢጭአት ዘገኛ ድርጅት ነው ፣ እንዳሉኝ ለስብሰባው ገለጽኩ ።

ከዚህ በኋላ ወደ አንደኛው የአጀንዳ ነጥብ አልፈን ለጽ/ቤቱ በአዋጁ መሠረት አንዱ የመኢሶን ተወካይ መምረጥ ስላለብን ይህ ሰው ማን መሆን አለበት በሚለው ላይ ተነጋገርን ፣ በዚህም ላይ አቶ ዳንኤል ታደሰ እኔ እንድሆን ሐሣብ አቀረበ ፣ ሌሎቹ ጓዶች ለምሣሌ ነገደ ጎበዜ ፣ አቶ አንዳርጋቸው አሰግድ፣ ዶክተር ተረፈ ወ/ጻዲቅ ጽ/ቤቱ ትልቅ ቦታ ስለተሰጠው ሁኔታውን በደንብ የሚያውቅና ዝርዝር ነገሮችን ለመከታተል የሚችል ሰው ይሁን የሚል ኃሣብ አቀረቡ ። አቶ ዳንኤል ቀደም ሲል ስለ እኔ መመረጥ

ኃሣብ ያቀረበው መስሰን ከጽ/ቤቱ ወጪ ማለት አለበት፣ ማለትም ከጽ/ቤቱ
ውስጥ ያሉት የመኢሶን ሰዎች ቁጥር መቀነስ አለበት ከሚለው ጋር ይሄዳል
በሚል ነበር ፤ ደግሞም የእኔ እዚያ መቆየት ሌሎችን ከጽ/ቤት ለማስወጣት
የታቀደ ኃሣብ ነበር ፡፡ ለማንኛውም ግን ሦስቱ ጓዶች ያቀረቡት ኃሣብ አሸ
ንፎ አቶ መስፍን ካሡ ለጽ/ቤቱ ተመ ረጠ ፡፡

* ከዚህ በኋላ ወደ ሁለተኛው አጀንዳ ነጥብ አልፈን እንደተነጋገር
ነው ስለ ፓለቲካ ት/ቤት ጓዱ አንዳርጋቸው አሰግዴና ጓዱ ንግስት አዳነ
በቋሚ መምህርነት መኢሶንን እንዲወክሉ ተመረጡ ፡፡ ቀጥሎም ጓዱ ታደሰ ገሠሠ
ከፖለቲካ ት/ቤት ወጥቶ ለደህንነቱ የማያሰጋው ማለትም ቀደም ሲል የፖለቲካ
ት/ቤቱ አስተዳዳሪ ስለነበር ኢ.ሕ.አ.ፓዎች ስለሚያውቁን አደጋ ከማይጥሉ
በት ሁኔታ ሥራ እንዲፈለግ ተወ ሰነ፤ ለዚህም ከተጠቆሙት የሥራ ቦታዎች
ምድር ባቡር ውስጥ፣ ገብቶ እንዲሰራ ኃሣብ ቀርቦ ነበር፤ ዳሩ ግን አልጸደ
ቀለትም ፤ ለፓለቲካ ት/ቤት የሪሰርች ክፍል ሁለት ሰዎች ይፈለጉ ተብሎ
ስለነበር በመጠሉ ግን የት/ቤቱን አቋም የሚወስን አዋጅ ስለወጣ በቀረቡት
ሁለት ሰዎች ጉዳይ ላይ የመኢሶን ስራ አስኪያጅ ከሚቴ := 1ኛ/ አቶ ሲሣይ
ታከለና 2ኛ/ ዶክተር ከበደ መንገሻ ከሕ/ድርጅት ጉዳይ ጽ/ቤት ጓዶች 1ኛ/
እኔ እራሴ ፤ 2ኛ/ አቶ መስፍን ካሡ ጋር በጉዳዩ እንድንነጋገርበት የተ
ወሰነ ያመስለኛል ፡፡ ለማንኛውም በአዋጁ መሠረት ለሪሰርች ክፍሉ የሚመረጡት
አባሎች ጉዳይ ቀር ቶአል ፡፡

ለኢፎትራ ክፍለ ሃገር ከአምስቱ የሕብረት ድርጅቶች ከእያንዳንዱ
ሁለት ካድሬዎች ይመደቡ ተብሎ ከሕብረቱ ተጠይቆ ስለነበር የሚመደቡትን ካ
ድሬዎች እኔና መስፍን ካሡ ፈልገን እንድናቀርብ ተወ ሰነ ፡፡ ነገር ግን ሰ
ዎች በማጣታችን ሳይመረጥ ቀረ ፡፡ ጽ/ቤቱም በሚመለከተው በኩል መስፍን ተ
መርጦ ነበር ፤ ዳሩ ግን ሊቀ መንበሩ እኔን ጠርተው መስፍን ካሡ ባይሆን
ይሻላል ሌላ ሰው ብትለውጡልን ስላሉ በመስፍን ካሡ ቦታ አንዳርጋቸው አሰ
ግዱ እንዲሆን ተደርጎአል ፡፡ እንደዚሁም ለፓለቲካ ትምህርት ቤት ዶክተር

../..

ንግሥት አቃነናና አቶ የራስ ወርቅ አደማሴ እንዲሆኑ ተወስኖ እነዚህ ጓዶች ሥራውን ጀምረውት ነበር ::

አቶ መስፍንም ለድርጅቱ ጽ/ቤት የማይስማማበት ምክንያት :=

ሀ/ አቶ መስፍን ከሰው ጋር የመግባባት ችሎታ ስሳሌለው ፣

ለ/ እዚህ ግጮ ውስጥ ሰዎች ስለማይወዱት ነው :: ሲሉ ሊቀ መንበሩ ገለጸውልኛል ::

ሐምሌ 17 ቀን 1969 ዓ.ም ከምሽቱ አንዱ ሰዓት ጀምሮ በአቶ ሲሣይ ታከለ ቤት ይመስለኛል አንዱ ልዩ ስብሰባ := 1ኛ/ አቶ መስፍን ካሱ ፣ 2ኛ/ ዶክተር ከበደ መንገሻ ፣ 3ኛ/ አቶ ኃይሌ ፊዳ ፣ 4ኛ/ አቶ ዳንኤል ታደሰ ፣ 5ኛ/ አቶ ሲሣይ ታከለ ሆነን :=

ሀ/ ስለ አቶ መስፍን ካሱ ተልክ

ለ/ ስለ ቺ. ፒ. ኤል.. ኤፍ ደብዳቤ መምጣት

ሐ/ ስለ ማሻግሻግ አጀንዳዎችን ይዘን መወያየት ቀጠልን ::

በመጀመሪያ አቶ መስፍን ካሱ ስላለለው ተልክ፣ ቀደም ሲል ከእኛ ጋር ግንኙነት ያደረጉት ኩ/ደሣለኝ እና በአቀረብነው ነጥቦች የሚስማሙ መሆናቸውን የገለጠልን ይመስለኛል ፣ ከዚህ በኋላ ዳንኤል ታደሰ በሚሊሻ ያ፣ 5ኛ ክፍለ ጦር ውስጥ ደህና የፓለቲካ ሥራ የምንሰራበትን ፕሮግራም ማዘጋጀት አለብን ብሏል :: ዶክተር ከበደ በበኩሉ የእኛ ጽሁፎች በዚህ ሠራዊት ውስጥ በብዛት እንዲሰራጩ እንደዚሁም የየሥራቸውን የጥናት ክበቦች እንዲያቋቁሙ እኛም በእነዚህ አማካይነት የፓለቲካ መስመራችንን በናስፋፋ እንደዚሁም አንዳንዱ የመኢሶን ሰዎች በሠራዊቱ ውስጥ ገብተው ቢያግዙን መልካም ነው ብሏል :: ቀጥሎም እዚሁ አዲስ አበባ ሆኖ ከሌሎቹ በየቦታው ከሄዱት የሠራዊቱ ክፍሎች ጋር ግንኙነት ቢቀጥል ጠንካራ ቡድን በመሥርቶ መልካም ነው :: የሚል ኃሣብ ከቀረበ :: እነዚሁ ነጥቦች ለኩ/ደሣለኝ እንዲተላለፉ ተወስኖ ወደሚቀጥለው አጀንዳ ተሻገርን ::

../..

2ኛው አጀንዳ የቲ.ፒ.ኤል.ኤፍ/T.P.L.F/ ጉዳይ ነበር

ቲ.ፒ.ኤል.ኤፍ የተባለው ድርጅት በዶክተር ከበደ መንገሻ በኩል ለመኢሶን ደብዳቤ ጽፎ መኢሶን ስለደርግ ስለብሔረሰቦች ጥያቄ ፣ ስለ አለም አቀፍ ኮሙኒስት ንቅናቄ እና ስለመሳሰሉት ጥያቄዎች ያለውን አቋም ለቲ.ፒ. ኤል.ኤፍ እንዲገልጽ ጠይቆ ስለነበር ፡=

1ኛ/ መልሱ በድርጅት ውስጥ ሳይሆን በግለሰብ ደረጃ እንዲጻፍላቸው

2ኛ/ መልሱ በፖሊሲዎቹ ጥያቄዎች ላይ እንዲያተኩር ፡=

3ኛ/ የመኢሶንን ስም እንዳያነሣ ተደርጎ እንዲጻፍላቸው ተወሰነ ፡

ቲ.ፒ.ኤል.ኤፍ./T.P.L.F./ ማለትም የትግራይ ሕዝብ ነፃ አውጭ ድርጅት ማለት ነው ፣ የሚገኘውም በትግራይ ክፍለ ሃገር ውስጥ ነው ፣ ማን እንደሚመራውና በተለይ የት በታ እንዳሉ አላውቅም ፣ በደብዳቤውም ላይ የተገለጸ ነገር አልነበረም ።

3ኛው የአጀንዳ ነጥብ ስለ ማሸግሸግ በጊዜ ማጠር ምክንያት ሳይነሣ ቀርቷል ።

በሚቀጥለው ቀን ሐምሌ 18 ቀን 1969 ዓ.ም ከምሽቱ አንድ ሰዓት ጀምሮ በአቶ ሲሣይ ቤት ፣ ከላይ የተጠቀሱት ሰዎች በሙሉ ሆነው አቶ መስፍን ስለ ተልኮው ሲያስረዳን ሰዎቹ በአቀረብንላቸው ተጨማሪ ኃሣቦች መስማ ታቸውን ገለጸልን ማለትም ኮ/ደሣለኝ ማለት ነው ። ከዚያም በኋላ በኢንፎ ርሜሽን ደረጃ አንደኛው የሚሸፍነው ክፍለ ጦር ለኤርትራ ፣ ሁለተኛ አምስ ተኛው ክፍለ ጦር በሐረርጌ ፣ ሦስተኛው ለትግራይ ፣ አራተኛው ለኤርትራ ሚ ሊሻ እንደሚሆኑ ገለጸልን ። ይህም ኢንፎርሜሽን የቀረበው በዚያን ጊዜ እነ ዚሁ ክፍለ ጦሮች በታጠቅ ሜዳ ውስጥ ስለነበሩ ፥ ከማሰልጠኛው ወጥተው የት የት እንደሚመደቡ ለማወቅ ብቻ ነበር ። ቀጥሎም አቶ ዳንኤል ታደሰ ወደ ሐረርጌ ክፍለ ሃገር ደህና ደህና ሰዎች መርጠን መላክ እንዳለብን እና እነሱም የመኢሶንን ሕቡዕ ሥራ ማጠናከር እንደሚያስፈልግ ገለጸ ። ከዚያም ወደ ልዩ ልዩ ጉዳዮች ታልፈና ዶክተር ከበደ መንገሻ ሌ/ኮ/ መንግሥቱ አን ደኛ ካድሬዎች በብዛት ለዘመቻው ስለመሰብሰቡ ፣ ሁለተኛ በሐረርጌና በሌሎች

..../...

ክፍለ ሃገሮች ስለታሰሩት ካድሬዎች እና ስለ ሕዝባዊ ድርጅቶች መሪዎች መ ፈታት ጥያቄ ማቅረብ እንዳለብን ። ሦስተኛ በአዋጁ መሠረት አዲስ የተቋቋመው መ/ቤት ማለትም የሕ/ድርጅት ጉዳይ ጽ/ቤት ሥራውን እስኪጀምር ድረጠ ለቀድሞው ጽ/ቤት መመሪያ መንግሥት እንዲያወጣ መጠየቅ እንደሚያስፈልግ ፡፡ በመጨረሻም፡= ሰፊው ሕዝብ ድምጽ ቁጥር 59 እንደገና ተባዝቶ እንዲጨመር ሃሣብ አቀረበ ። በዳኩሜንቱ ላይ ለከለል ቢሮ ለጠረርጌ ክለል ጠንካራ ሠራተኞች እንዲቀርብ የሚለው የሲሣይ የራሱ ማስታወሻ ይመስለኛል እኔ ምንም የማውቀው ነገር የለኝም ። ስብሰባው ከመበተኑ በፊት ለሚቀጥለው አጀንዳ፡=

1ኛ/ ስለ ሶማሊያ ወረራ

2ኛ/ በቅርቡ ስለሚወጣው የከተተ አዋጅ መኢሰን አቋም መውሰድ ስላለበት ይኸው በአጀንዳ እንዲያዝ አሣስቤ ስብሰባው ተበተነ ።

ሐምሌ 20 ቀን 1969 ዓ.ም ከምሽቱ 1 ሰዓት ጀምሮ እ-ኔ ቤት በነበረው የፖለቲካ ቢሮ ስብሰባ ተካፋይ የነበሩት፡=

1ኛ/ አቶ ዳንኤል ታደሰ
2ኛ/ ,, እንዳርጋቸው አሰግድ
3ኛ/ ,, በርሃኑ ገመዳ
4ኛ/ ,, ኃይሉ ፊዳ
5ኛ/ ዶክተር ተፈራ ወ/ ጻዲቅ
6ኛ/ ,, ከበደ መንገሻ
7ኛ/ ,, ነገደ ጎበዜ
8ኛ/ አቶ መስፍን ካሱ
9ኛ/ ,, ሲሣይ ታከለ ሲሆን የስብሰባው አጀንዳ መስፍን ካሱ ለጽ/ቤቱ በመመረጡ እነ ሌ/ኮ/ መንግሥቱ አልተደሰቱምና ይቀየር ብለሉን በዚሁ ላይ ለመነጋገር ነበር ። የስብሰባውን አጀንዳዎች ከመነጋገራችን በፊት ዜናዎችን ተለዋውጠናል ። እነዚህም ዜናዎች ፡=

.../...

1ኛ/ ከሚልሽያው ሠራዊት ውስጥ አንዳንድ ብርጌድ በሸዋ ፣ በአ ሩሲ ፣ በባሌ ፣ በሲዳሞ በጋሞ መልክ እንደሚመደቡና እን ደዚሁም ሶማሊያ እንዳደረገቻው ሁሉ የኢትዮጵያ መንግሥትም በበኩሉ ሰርጎ ገቦችን ወደ ሶማሊያ ለመላክ እንዳሰበ ::

2ኛ/ አንድ የመኢሶን በራሪ ወረቀት ፔቲ ኦፊሰር ታምራት አጼ ገብ ቶአል እንደሚባል፣

3ኛ/ በቀበሌው ውስጥ የተመረጡት ሰዎች የመኢሶን አመራር ሊያሽ ጡርሰን ነው እንደሚሉና በአባላት በኩል በቀበሌው ጉዳይ ላይ፡ ቅሬታ እንዳሉ ይህም ማለት ጊዜአዊ ወታደራዊ መንግሥት፡ ቀበሌዎችን በጊዜው ባለማስታጠቅ ቀበሌዎች እናመልከት ሲሉ የመኢሶን አመራር አይዘአቸሁ ዝግ ብሉ ስላላቸው ነው ብሉ

4ኛ/ በመምህራን አካባቢ ከፍተኛ ስጋት እንዳለ እና ይኸውም ስ ጋት የመጣው ከመኢሶን ጋር መያያዝ ሞትን የሚያስከትል እ ንደሆነ፡ አድርገው ስለወሰዱት መሆኑ ነው :: በዚህ ጥያቄ ላይ በሌላ ጊዜ የአሰራራችን ጉዳይ ለውይይት ሲቀርብ እን ነጋገርበት ተባለ ::

5ኛ/ ደርግ ከእስር ቤት ውስጥ፣ ካሉት የኢ.ሕ.አ.ፓ ሰዎች ይመ ለምሳሌ ማለትም ወደ ሰደድ ድርጅት በማስገባት ላይ ነው የሚል ወሬ እንዳለ ::

6ኛ/ የሕ/ድርጅት ጉዳይ ጽ/ቤት ካድሬዎች ስብሰባ ተደርጎ ብዙ ኃኑ ወደ ጦር ግንባር እንዲሄዱ የማድረግ ሃሣብ እንዳለ::

7ኛ/ በናዝሬት አካባቢ የመኢሶን አባላት ከሁለት ተከፍለው እርስ በእርስ እየተጣሉ ናቸው የሚል ወሬ እንደሚነፍስ ነው ::

8ኛ/ አንዳንድ አባላትን ከአደጋ የመጠበቅ ጉዳይ ተነስቶ ይህንን ጉዳይ በሌላ ጊዜ በአጠቃላይ እንድንወያይበት ነው::

፱ኛ/ ሌ/ኰ/መንግሥቱ ወደ ሐረር ክፍለ ሃገር በነበሩ ጊዜ ከጠሩ
የ17 ነጥብ ጥያቄዎች ቀርበውላቸው ነበር ፣ የሚል ዜና
ደርሦን በተለይ ጓዱ ዳንኤል ታደሰ ከሌ/ኰ/ መንግሥቱ
ጋር አብረው ሄደው ስለነበረ የዚህን ዜና እውነተኛነት ስለ
ተጠረጠረ ኢንፎርሜሽኑ ይጣራ ። በሚል ታለፈ ይሁንና ይህንን
ኢንፎርሜሽን በኋላ እንኳን ለማጣራት አልተቻለም የሚል ተ
ለዋወጥን ።

እነዚህን ከአንዱ እስከ ዘጠኙ የተዘረዘሩትን ዜናዎች ከተለዋወጥን በኋላ ወደ አጀንዳው ነጥብ ስናልፍ እኔ ሌ/ኰ/መንግሥቱ ጠርተውኝ በመስፍን መመረጥ እንዳልተደሰቱና ሌላ ሰው እንደመረጥ እንደጠየቁኝ ገለጸኩኝ ። ከዚህ በኋላ የሰበሰባው ተካፋዮች ከዚህ እንደሚከተለው ኃሳባቸውን ሰጡ ፡፡

<u>ዶክተር ተረፈ ፡=</u> መኢሶን ጠንካራ አመራር እንዳለው ማሳየት ያስ
ፈልጋል ይህንንም ለማድረግ የሚቻለው በአስቸ
ኳይ የድርጅቱን ጠቅላላ ጉባኤ በመጥራት ነው ።

<u>ዶክተር ከበደ ፡=</u> ወደ መጣንበት ጉዳይ እንመለስ ፣ ጥያቄው ከን
ኘሮምማይስ እናድርግ ወይስ በዚያው በመጀመሪያው
ምርጫችን እንርጋ የሚል ነው ።

<u>አቶ ዳንኤል ፡=</u> የአቶ ኃይሌና የአቶ ነገደ ከሕ/ ድርጅት መው
ጣት አባላትን አስደስቷል ። ደግሞም እነርሱ /
ማለትም ሰደደች/ የሚሉትን ዝም ብለን መቀበል
የለብንም ።

<u>ዶክተር ነገደ ፡=</u> አቶ መስፍን እንደሚለውጥም በጉል ከነርሱ ጋር
ቀጥታ ግጭት ውስጥ መግባት ይሆንብናል፣ ደል ቀንጡ
መስፍንን እንሰውጠውና በእኛም በኩል ከማሌሬዱ
አበበ እንዲገባ እንጠይቅ ።

<u>አቶ ብርሃኑ ፡=</u> ይሄ ከተባለው እነርሱም አገሌ ይግባ ብለው ሲ
ጠይቁን ስለሚችሉ አያዋጣም ።

አቶ ቢሣይ ፡= የዶርዶች ነፃነታችንን እንጠብቅ /ማለትም መስፍ ንን አንለወጠውም/

ዶክተር ከበደ ፡= ነገሩን በደንብ እናመዛዝን ይህንን ኮምፕሮም ማይዝ ማድረጉ ጊዜ ይገዛልናል /ማለትም መሿቡን በቀርጡ ይመጣል ተብሎ ስለነበር ጊዜ እናገኛ ይ ሆናል በማለት ነዉ ፡፡

አቶ መስፍን ቢሶ ፡= ይኼ የሚጎዳን ኮምፕሮማይዙስ አይደለም ፡፡ ነገር ግን ኃይሉ ፣ ነገደና ከበደ በምርጫው ውስጥ አይገቡበትም ፣ ማለትም ለጸ/ቤቱ አይመረጡ ፡፡

አቶ ኃይሉ ፊዳ ፡= ኮምፕሮማይዝ ማድረጉ ጥሩ ነው በተለይም አሁን በሃሣብ በተዋጡበት ወቅት ኮምፕሮማይዝ አለማድረጉ አ ያዋጣም ፡፡

ዶክተር ተረፈ ፡= ኮምፕሮማይዝ እናድርግ ይህንን ማድረግ ግልጽ ነው ፡፡

አቶ አንዳርጋቸው ፡= እርሱን ማለትም መስፍንን ሊተካ የሚችል ሰው ማነው ?

አቶ ዳንኤል ታደሰ ፡= አስተሳሰባችን በጭራሹ ልክ አይደለም፣ ሰበብ የምንፈልግ ይመስላል / ማለትም ኮምፕሮ ማይዝ ላማድረግ ሰበብ የምንፈልግ ይመስላል ማለቱ ነው/፡፡

ዶክተር ከበደ ፡= እነሱ ካልፈለጉት ለመቀትም ይችላሉ ፡፡ ደግሞ በዚች ኮምፕሮማይስ በማድረግ ከፍተኛ አደጋ ለ ናስወግድ እንችላለን ፡፡

ዶክተር ተረፈ ፡= የሬትሪት /የማሸግሸግ/ ነገር ሲታሰብ ሰዎቻ ችንን በደንብ ሪድፕሎይ/ ማለትም በቦ በታ ማጠያዝ/ ማድረግ ያስፈልጋል ፡፡ ስለዚህ የጸ/ቤቱን ሥራ የሚ ያቅ ሰው ከዚያው ከጸ/ቤቱ ይፈለግ ፡፡

../...

<u>አቶ ዳንኤል</u> ፡= እዚህ ከተሰበሰብነው ሰዎች ውጭ ሌላ ሰው ማዱረግ አንችልም ።

<u>አቶ አንዳርጋቸው</u> ፡= ከሣሁን ሊሆን የሚችል ይመስለኛል /ከሣሁን የሚለው የወለጋ ክፍለ ሃገር የሕ/ዴ/ጉ/ጽ/ቤት ቅርንጫፍ ም/ እና በወቅቱ በሐረር ክፍለ ሃገር መኢሶንን ወክሎ የተመደበውን ጓድ ማቀረቡ ነው/።

<u>ዶክተር ተረፈ</u> ፡= ጽ/ቤቱ ብዙ ፖዚቲቭ ሥራዎችን ላይ ሰራ እንዲያውም ብዙ ነጌቲቭ ሥራዎችን ሊሰራ ይችላል ። ስለዚህም መስፍንን የሚተካው ሰው በዚህ አንጻር እናስበው ሲል ሃሣቡን እንደሰነዘረና እንደጨረሰ ከላይ በአጠቃላይ እያንዳንዱ የስብሰባው ተካፋይ የሰጡትን ፍሬ ነገር መሠረትነ በማድረግ ብዙሃኑ ኮምፕሮማይስ እንቀበል ሲሉ አቶ ዳንኤል ታደሰና አቶ ሲሣይ ታከለ ተቃውሞው ስብሰባው ኮምፕሮማይስ መቀበሉን ሃሣብ አጸደቀው ።

ከዚህ በኋላ ውይይቱ እንደገና ቀጥሎ ዶክተር ነገደ እኛም ተስፋዬ መኮንንን ይኑሣ ብለን እንጠይቅ አለ ። መስፍን ካሱ ይህንን እንጠይቅም በድርጅቶች ነፃነት ውስጥ አንገባ ካለ በኋላ ከነገደ በስተቀር ሁሉም የተስፋዬ ስም አይጠቀስ ፤ በሚለው ተስማምተው ነገሩ ተዘጋ ። ከዚህ በኋላ አቶ ዳንኤል ታደሰ ስለማሬዳች ጉዳይ በሌላ መድረክ እንድናነሣ ሃሣብ አቀርበ በሙሉ ድምጽ አቶ አንዳርጋቸው አሰግዱ መስፍን ካሱን እንዲተካው ተወሰነ ። ይህንን ውሣኔ ከማስታወቃችን በፊት ግን ትንሽ ጊዜ እንጠይቅ ተባለ፤ ስብሰባውም በዚሁ አበቃ ።=

ሐምሌ 24 ቀን 1969 ዓ.ም ከምሽቱ 1 ሰዓት ጀምሮ ምናልባት በእኔ ቤት ወይም በአቶ ሲሣይ ቤት ሣይሆን አይቀርም ፣ ለጊዜው ላስታውሰው አልቻልኩም ፣ በስብሰባው ተካፋዮች የነበሩት ፡=

1ኛ/ ዶክተር ነገደ ጎበዜ
2ኛ/ ,, ተረፈ ወ/ጻዲቅ
3ኛ/ አቶ ሲሣይ ታከለ
4ኛ/ ዶክተር ከበደ መንገሻ
5ኛ/ አቶ አንዳርጋቸው አሰግድ
6ኛ/ ,, መስፍን ካሡ
7ኛ/ ,, ዳንኤል ታደሰ
8ኛ/ ,, ኃይሉ ፊዳ ናቸው ።

የስብሰባችን አጀንዳ ፡=

1ኛ/ ስለ ጓዱ አብዱላሂ ቀብር
2ኛ/ ,, ሕብረት ኮሚቴዎች ሰዎችን መመደብ ፣
3ኛ/ ለኤርትራ ካድሬዎችን ስለመመደብ ፣
4ኛ/ ስለ ጠቅላላው አሰራራችን ፣
5ኛ/ ,, ውጭ ጉዳይ ኮሚቴ ፡= በዳኩሜንቱ ላይ "ለተከሌ ሥራ መስጠት / በተስፋ በኩል/ የመኢሶን አባል ነው" የሚለው ምን እንደሆነ አላውቅም አቶ ሲሣይን መጠየቁ የሚሻል ይመስለኛል ።

በመጀመሪያ ዜና ስንለዋወጥ አዋሬ በቦንብ ተደብደባለች የሚል ለጊዜው የማላስታውሰው ከተሰብሳቢዎች መካከል ኢንፎርሜሽን ሰጠን ። አዋሬ ማለትም በኦጋዴን አውራጃ ደገሐቡር አጠገብ ያለ አንዱ ከተማ ነው፣ ከዚህ በኋላ ወደ አቶ አብዱላሂ ሞት ጉዳይ አለፈን ዶክተር ነገደ ጎበዜ አብዱላሂ የተገለጸው ከቤተሰቦቹ ጥያቄ ጋር በተያያዘ ሁኔታ ነው ። በሰፊው ሕዝብ ድምጽ ወይም በተርካኙ ላይ ስለ ቤተሰቦቹ መብትና ስለ ነፍጠኛው መታጠቅ

ጽሁፍ ይውጣ ። ይህንንም የመጽሔቱ በርቱ ያወጣው ስለ ። ከዚያም ዶክተር ተረፈ አብዱላሂን ከጠረር ከተነሣ በኋላ ለምን ገደሉት? የሚል ጥያቄ አቀረበ ፣ ስለ ገዳዩች በጊዜው የተወሰደው ግምት የብሔር ትምክተኞች ማለትም በጠረር ነፍጠኞች ናቸው የሚል ነበር ። ዶክተር ነገደ የዶክተር ተረፈን ጥያቄ ሲመልስ አብዱላሂን የገደሉት ወደዚያው ወደ ጠረር እንዳይመለስባቸው ፈርተው ነው ። እዚያ ተቀባይነት እንዳለው አውቀው ነው ። ከዚህ በኋላ የቀበሩን ዝግጅት የሚከታተል ኮሚቴ አቶ መስፍን ካሱ ፣ ዶክተር ነገደና አቶ ጀማል ያሉበት ተቋቋመ ። ይህንን እንደጨረስን ወደ ሁለተኛው አጀንዳችን ፡ ተሳለፈን ለሕብረት ማስታወቂያ ኮሚቴ ዶክተር ነገደ እንዲመደብ ለውጭ ጉዳይ ኮሚቴው ደግሞ እኔ ራሴ እንድሆን ተወሰነ ።

ለሕዝባዊ ሠራዊት ኮሚቴና ለኢኮኖሚ ኮሚቴ ሰዎችን በመፈለግ ላይ እንደሆን ለሕብረቱ ጉባኤ እንዲነገር ተወሰነ ። ከዚያ ወደ ሦስተኛው አጀንዳ ተሳለፍን በዚህም አጀንዳችን ላይ መግቢያ አስር ሺህ ወዛደሮች ለኤርትራ ይመረጣሉ የተባለው ኢንፎርሜሽን እንዲጣራ ምናልባት ሲሰራ ይመስለናል ለስብሰባው ካሣሰብን በኋላ ሕብረቱ በጠየቀው መሠረት ሁለት /ሰዎችን/ ካድሬዎችን ወደ ኤርትራ በሰመላክ ውይይት ቀጥሉ ዳንኤል ታደሰና አቶ መስፍን ካሱ ፣ ዶክተር ነገደ ጎበዜና እኔ እራሴ ፣ ዶክተር ተረፈ ፣ ዶክተር ከበደ እና አቶ እንዳርጋቸው አሰግድ የተጠየቀትን ሁለት ሰዎች እን[illegible] ባለን በኋላ ዶክተር ተረፈ ከራይስስ አለብን /ማለትም የካድሬዎች እጥረት አለብን/ በማለት አሣሰቡን ። በመጨረሻም ዶክተር ከበደ በተወሰነው መሠረት ሁለቱ ሰዎች ተመርጠው እንዲዘጋጁ አሣሰበው ወደ አራተኛው የአጀንዳ ነጥብ አለፍን ፣ ይኸውም ስለ አሰራራችን ሲሆን ዶክተር ከበደ በዙዎቹ ጓደኞች ምንምጥንቃቄ እንደማያደርጉ እና አሰራራችንን ማሻሻል ማድረግ እንዳለብንና ጥንቃቄም መልመድ እንዳለብን አሣሰበን ፣ ከዚያ በኋላ አቶ እንዳርጋቸው በራሱ ላይ ሂስ ሲቀርብ አንተ ራስህ ቤትህን በደንብ ማደራጀት አለብህ አለው ። ።

ይህንንም ማለቱም ዝብጃቶች ስለሚበዙና ቤቱ በማንኛውም ሰዓት ለ
ማንኛውም ሰው ክፍት በመሆኑ ነው ። በመጨረሻም በውሣኔ መሰክ ዶክተር
ከበደ እኔ እራሴና ዶክተር ነገደ ትራንስፖርትን በሚመለከት በኩል አንዱ
ላይ አብረን እንዱን ሄዱ ተወሰነ ። ይህም የሆነበት ለሲኩሪት ታስቦ ነበር ።
አሁንም ከአርእስቱ ውጭ በሀመራ ስለተገደሉት አራት ባዱሬዎች በሰፊው ሕዝብ
ድምጽ ላይ ጽሁፍ እንደወጣ ዶክተር ነገደ አሣሰበ ፣ ከዚያም ወደ መጨረሻ
ው ማለትም ወደ አምስተኛው አጃንዳችን ተሳልፈን ስለውጭ ግንኙነታችን ከተ
ነጋገርን በኋላ አንደኛ ከሶቪየት ሕብረት ጋር ጊዜያዊ ዱጋፍ እንደናገኝ
መጣርእንዳለብን፣ ሁለተኛ ከቻይና ጋር የጠበቀ ግንኙነት ማዱረግ እንዳለብን፣
ሦስተኛ የተራማጅ ሐገሮች /የውስጥ ጠ/ የውስጣዊ ጠባይ ማንነትና ከነዚህም
ሐገሮች ጋር የበለጠ ግንኙነት ማዱረግ ስላለብን ፣ አራተኛ በሺኩቴ ፣ በ
ጅዱጋ ፣ በዱሬደዋ፣ በአሣይታ፣ በኤደን ፣ የውጭ ግንኙነትን ለመፍጠርና
ለማካሄዱ የሚችሉ ሰዎችን ማስቀመጥ እንዳለብን ውሣኔ ተደረገ ይሁንና እነዚህ
ን ውሣኔዎች ከሥራ ላይ ለማዋል አልተቻለም ።

እነዚህ በታዎች ከሌሎቹ የመረጥንበት ምክንያት ወደ ቀይ ባሕር
ስለሚጠጉና ወደ ውጪ ለመመለስም በጣም ቀላል ስለሆነ ነው ። ከሥራ ላይ ባ
ለማዋል ችግር የፈጠረብን የጊዜ አጥረትና የመሸሽ ጥዱፉያ ስለመጣ ነበር፣
ለማንኛውም ለሚቀጥለው ስብሰባችን ዶክተር ተረፈ ስለውጭ ጉዳይ ኮሚቴው ሥራ
ሪፖርት እንዲያደርግ ተጠየቀ ። ከዚህ ላይ ለመጨመር የምፈልገው ከደበብ
የመን፣ ከኪውባ ፣ ከቻይና በመጠኑም ከሰሜቱ ሕብረት ኤምባሲዎች ጋር
ጥሩ ግንኙነት እንደነበረን ነው ። እነዚህ ኤምባሲዎች የዱርጅታችንን የፓ
ለቲካ መስመር በደንብ የሚያውቁና የሚከታተሉ እንደዚሁም የሞራል ዱጋፍ ሲ
ሰጡ የቆዩ ናቸው ። ከዚህ ውጭ ግን ምንም ግንኙነት የለንም ።

ውይይቱ ቀጥሎ አቶ ዳንኤል ታደሰ ስለ ዓለም ሁኔታ ለዱርጅቱ አ
ባላት ትንተና የሚያቀርበው የውጭ ጉዳይ ኮሚቴው ነወይ? ሲል ጥያቄን አቀ
ረበ ፣ ለዚህም ዶክተር ከበደ ሸመሊስ ትንተናን የሚያቀርበው የመጽሔት

፡ዶና የውጭ ጉዳይ ከሚቴ በጋራ መሆን እንዳለበት አስረድቶ ፤ ነገር ግን
ዓለም ሁኔታ ትንተና ከተደረገ የቆየ መሆኑን ገለጸ ። ከገለጸውም ውስጥ
ነበሩት ነጥቦች ስለ አሜሪካን ኢንፒር ያሊዝም ፤ ስለ ሶቪየት አገሮች ፤ ስለ
ነት እንቅስቃሴዎች በጠቅላላውም በዓለም አቀፍ ደረጃ ስለ ጦይሉ አስ
ጽፍ ነበር ። በመጨረሻም ደክተር ነገደ የሺርጀቶ አባላት በሙሉ ስለ
ም ሁኔታ ውይይት እንዲያደርጉ መመሪያ ይተላለፍ ቢሉ፡ ሃሣቡን ሰንዘር
ዝበሰቧቸን፡ ፍጹም ሆነ ፤ የነበረን የሰበሰቡ፡ ውይይቶች እነዚህ ነበሩ
የአምነት ቃሉን ሰጥቶ ፈረምኩኝ ።==